የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት

ሞጁል ሶስት

አዘጋጆች፡- ተገኔ ጌታነህ
ከድር መሀመድ

የፍትህ አካላት ባለሞያዎች የስልጠና ማእከል
የወረዳ ዳኞች እና ዐ/ሕግ ስልጠና ፕሮግራም

ነሐሴ 2000
አዲስ አበባ

ማውጫ

ገጽ

አጎጽሮተ ቃላት ii

መግቢያ 1-2

1. ዋስትና 3-11

2. የጸረ ሙስና ልዩ ሥነ ሥርዓት ሕግ 12-16

3. የደንብ መተላለፍ ወንጀል ሥነ ሥርዓት 17-21

4. በወንጀል ነገር ገብተው የተገኙ ህጻናት የፍርድ ሒደት/Children in Conflict with the Law/ 22-28

5. ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክስን መስማት 29-32

6. የይግባኝ ሥነ ሥርዓት 33-39

7. ቅጣት፣ ገደብ እና አመክሮ 40-48

ዋቢ ጽሁፎች 49

አጎጽሮተ ቃላት

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ	ኢ.ፌ.ዲ.ሪ
የወንጀል ህግ አንቀጽ	የወ/ሕ/አ
የወንጀል ህግ ሥነ ሥረዓት ቁጥር	

መግቢያ

በዚህ ሶስተኛው ና የመጨረሻው የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓትን በተመለከተው ክፍል ውስጥ የተካተቱት ነጥቦች ዋሰትና፣ ከመደበኛው ክስ መስማት ሂደት በተለየ ሁኔታ የሚስተናገዱ ጉዳዮች፣ ይግባኝ፣ ገደብ እና አመክሮ ናቸው። ልዩ ሥነ ሥርዓትን የሚከተሉት የጸረ ሙስና ጉዳይ፣ ደንብ መተላለፍ፣ ህጻናት በወንጀል ነገር ገብተው ሲገኙ የምንከተለው ሥርዓት እና ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ጉዳይን መስማት ናቸው።

ሰልጣኞች ቀደም ብሎ በሞጁል አንድ መግቢያ ላይ በተገለጸው መልኩ የሀገራችን የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ዝርዝር ጉዳዮችን ያላካተተ መሆኑን ተገንዝበው የሚነሱ የተለያዩ የህግ ትርጉም ጥያቄዎችን ለህጉ በአግባቡ በህገ መንግሰቱ እና በኢትዮጵያ በጸደቁ አለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት ትርጉም በመስጠት ስራ ላይ ማዋል ይጠበቅባቸዋል።

ያለው ህግ የራሱ ክፍተቶች ቢኖሩትም በህግ አውጪው አካል እስኪሻሻል እንዳለ በስራ ላይ ቢውል በርካታ ችግሮችን ሊቀርፍ እንደሚችል በተግባር የተረጋገጠ ነው። ህጉ በብዙ መልኩ ዘመናዊ እና ሊያሰራ የሚችል ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገራችን የተደረጉት የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ እንቅስቃሴዎች የሚያረጋግጡትም ይህንኑ ሀቅ ነው። ለረዥም ጊዜ የህጉ መሰረታዊ ድንጋጌዎች ተዘንግተው በመቆየታቸው የፍትህ መዘግየት ተከስቶ ነበር። ህጉ ይሻሻላልም ማለት ፍጹም አዲስ የሆነ ስርዓት ይዘረጋል ማለትም አደለም። በዋነኛነት ግልጽነት የጎደላቸውን ና ክፍተት ያለባቸውን የሚያስተካክል ነው የሚሆነው።

የወንጀል ህግ ሥነ ሥረዓታችን ውስብስብ እና ቀላል ጉዳዮችን ነጣጥሎ ነው የሚመለከተው። በአለም ላይ ተቀባይነትን ባገኘው ለቀልጣፋ እና ውጤታማ የወንጀል የፍትህ ስርዓት የሚያግዘው አሰራር ጉዳዮችን እንደየ ልዩ ባህሪያቸው ለያይቶ ማስተናገድ ነው። ይህም differentiated case management ወይም በአህጽሮተ ቃል DCM በመባል ይታወቃል። በዚህ ክፍል በተለይ እንደምንመለከተው ህጋችን ጉዳዮችን

ያላቸውን ለየት ያለ ባህሪ ከግምት በማስገባት በተለያየ መንገድ እንዲስተናገዱ ይደነግጋል።

በመሆኑም ሰልጣኞች የወንጀል ህግ በስራ ላይ ውሎ የህጉን ዓላማ እውን በማድረግ የህብረተሰቡን ህልውና ለማስጠበቅ እና በሂደቱም የተጠርጣሪ መብት እንዲከበር የተዘረጋውን የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ተገንዝበው በሀገራችን እየተካሄደ ያለውን ሁሉ አቀፍ የፍትህ ማሻሻያ እንቅስቃሴ በሚያግዝ መልኩ መስራት ይጠበቅባቸዋል።

1. ዋስትና

የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ክፍለ ትምህርት በስተመጨረሻ ሰልጣኞች፡-

- ዋስትና ከሰብኣዊ መብት ጋር ያለውን ግንኙነት አውቀው ለተግባራዊነቱ በጽናት ይሰራሉ፤
- ዋስትና የሚፈቀድባቸው እና የሚከለከልባቸውን ምክንያቶች የተነትናሉ፡፡

<u>መርህ</u>፡- የዋስትና መብት ማግኘት ለአንድ በወንጀል ለተጠረጠረ ሰው የተሰጠ በዓለም አቀፍ ድንጋጌዎችም የተደገፈ መብት ነው፡፡ ይህ መብት በሀገራችንም ሕገ መንግስታዊ መሠረት ያለው ነው፡፡ የዚህን መብት በተመለከተ በሀገራችን ያለውን ህግ እና አተገባበሩን እንመለከታለን፡፡

የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 17/2/ ማንኛውም ሰው በህግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም ይላል፡፡ የዋስትና መብት ጥያቄ የሚነሳው አንድ ሰው ነፃነቱ በእስር ምክንያት ሲገደብ በመሆኑ በቅድሚያ አንድ ተጠርጣሪ ሊታሰር የሚችልባቸውን ምክንያቶች መመልከት ይገባል፡፡

በሕገመንግስታችን እንደተመለከተውና በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ላይ በዝርዝር እንደተቀመጠው ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች ሊታሰሩ ይችላሉ፡፡ አንድ በወንጀል ተጠርጥሮ የተከሰሰ ሰው በመከሰሱ ብቻ ሊታሰር ይችላል፡፡ ይህ የሚሆነው የተከሰሰበት ወንጀል በዋስ የማያስለቅቀው መሆኑ የተደነገገ ከሆነ ነው፡፡ በወንጀል ተከስሶ ወንጀል መፈፀሙ በማስረጃ የተረጋገጠበት ሰው ጥፋተኛ በመባሉ ሊታሰር ይችላል፡፡ ቅጣት የተወሰነበትም እንዲሁ ከዚህ በተጨማሪ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 ሥር በተደነገጉት ምክንያቶችም አንድ ተጠርጣሪ የዋስ መብት እንዳያገኝ ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡

አንድ ሰው በመከሰሱ ብቻ ሊታሰር ይችላል ካልን ክስ ቀርበ የሚባለው መቼ ነው? በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ ሁለተኛ መጽሐፍ ክፍል 1 ክስና አቤቱታ ስለማቅረብ በሚለው ሥር ቁጥር 11 ማንም ሰው ወንጀል ሲሰራ ያየ ወይም ያላየም ቢሆን የወንጀል ክስ እንዲቀርብ የማሳወቅ መብትና ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል። በቁጥር 13 ሥር ደግሞ ተበደልሁ ባይ ወይም ወኪሉ የክስ አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችሉ ያሣያል የወንጀል ክስም ሆነ የክስ አቤቱታ ለፖሊስ ወይም ለዓ/ሕግ ይቀርባሉ (ቁ. 16/1/) ለዓ/ሕግ ከቀረበ (ክሱ ወይም የክስ አቤቱታው/ ምርመራው እንዲካሄድ ለፖሊስ ማስተላለፍ አለበት/16/2/) ፖሊስ በቁ. 22 እና ተከታዮቹ መሠረት ምርመራውን በሚያካሂድበት ሂደት ተጠርጣሪውን የሚይዝበት ሁኔታዎች አሉ። ስለዚህ አንድ ተጠርጣሪ የክስ አቤቱታ ለፖሊስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮም ሊታሰር ይችላል ማለት ነው። በዚህ ጊዜ የታሰረውን ተጠርጣሪ ፖሊስ የዋስትና ወረቀት አስፈርሞ ካልለቀቀው (ቁ. 28) ተጠርጣሪው የዋስ መብቱ እንዲጠበቅለት ለፍ/ቤት ማመልከት ይችላል (ቁ. 28/2/)

የሕገ መንግሥታችን አንቀጽ 19(3) የተያዘ ሰው በ48 ሰዓት ውስጥ ፍ/ቤት መቅረብ እንዳለበት እና ለመታሠር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ሊገለጽለት እንደሚገባ ይደነግጋል። የወ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ. 29ም ተመሳሳይ ድንጋጌ አለው በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ፍ/ቤት ያልቀረበ ተጠርጣሪ ፍ/ቤት የአካል ነፃነቱን እንዲያስከብርለት ሊጠይቅ ይችላል። (ሕገ መንግሥት አንቀጽ 19/4) ከዚህም በተጨማሪ የሕገ መንግሥት አንቀጽ 19(6) የተያዘ ሰው በዋስ የመለቀቅ መብት እንዳለው ያሳያል። ይህ በመርህ ደረጃ የተቀመጠ በዋስ የመፈታት መብት ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 17 ጋር ተገናዝቦ ካልታየ የተሳሳተ ድምዳሜ ሊያደርስ ይችላል። ምክንያቱም በዋስ የመፈታት መብት በሕግ በተቀመጡ ምክንያቶች ሊገደብ ይችላልና ነው።

የወንጀል ተጠርጣሪ ስለሚያዝበት ሁኔታ

በመርህ ደረጃ አንድ ሰው ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊያዝ ወይም ሊታሰር አይችልም። (የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 49)። ይህ መርህ በሕገ መንግሥታችን አንቀጽ 17 ላይ በግልጽ ተቀምጧል። ነገር ግን በሕገ መንግሥቱም እንደተጠቀሰው (17.2) ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተጠርጣሪን ለመያዝ ሕግ በፈቀደ ጊዜ መያዝ ይቻላል።

ማንኛውም ሰው ወይም ፖሊስ ከ3 ወር በማያንስ ቅጣት የሚያስቀጣ ወንጀል ሲፈፀም የተገኘን ሰው (እጅ ከፍንጅ) ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ መያዝ ይችላል የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 50 መሰረት ፖሊስ ደግሞ ከአንድ ዓመት የማያንስ ቅጣት የሚያስቀጣ ወንጀል ለመሥራት የተዘጋጀን ሰው፣ ሰርቷል ተብሎ በሚገባ የተጠረጠረን ሰው፣ የሕዝብን ፀጥታ በማበላሸት ላይ የሚገኝን ሰው፣ ፖሊስ ሥራውን በሚሠራበት ወቅት የሚከላከለውን ሰው፣ ለማምለጥ የሞከረን እስረኛ፣ ከፖሊስ ወይም ከወታደርነት የከዳን ሰው፣ ሕግ ያልፈቀደለትን የቤት መሠርሠሪያ ይዞ የተገኘን ሰው፣ የተሰረቀ ዕቃ የያዘ ሰው፣ ወይም ወንጀል በመፈፀም ረገድ ያገኘው ዕቃ በይዞታው የተገኘበት ሰው፣ አደገኛ ሥራ ፈት መሆኑ የተጠረጠረን ሰው፣ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ መያዝ ይችላል (የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.51(1))።

ሌሎች በሕግ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት ለምሣሌ የፀረ ሙስና ኮሚሽን፣ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ አንድን ተጠርጣሪ መያዝ ይችላሉ። (51/2/)

ፖሊስም ሆነ ሌሎች ተጠርጣሪን ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ለመያዝ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት ተጠርጣሪውን በ48 ሰዓት ውስጥ ፍ/ቤት የማቅረብ ግዴታ ግን አለባቸው (የፀረ ሙስና አዋጅ ቁ. 235/93 አንቀጽ 7/6/) ከ48 ሰዓት በላይ ለማዘግየት የሚቻለው ተጠርጣሪውን በአቅራቢያው ወደ ሚገኝ ፍ/ቤት ለማቅረብ የቦታ ርቀትና የመገናኛ ሁኔታ ከገደቡ ብቻ ነው (የህገ መንግስቱ አንቀጽ 19/3/; የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 29/1/።

የዋስትና ወረቀት አስፈርሞ ስለመልቀቅ

ከላይ እንደተገለፀው ፖ/ሊስ የያዘውን ተጠርጣሪ በዋስ ሊለቀው ይችላል፡፡ ይህን ለማድረግ ወንጀሉ በጽኑ እሥራት የማያስቀጣ ሊሆን ወይም ደግሞ ተጠርጣሪው ወንጀሉን ለመፈፀሙ አጠራጣሪ ሆኖ መገኘት ይኖርበታል (የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.28)

ፖ/ሊስ በወንጀል ጠርጥሮ በመያዝ ለፍ/ቤት ያቀረበውን ተጠርጣሪ ፍ/ቤቱ በዋስትና ወረቀት ሊለቀው ይችላል (59/1/)፡፡ ይህን የሚያደርገው ተጠርጣሪው የተከሰሰበት ወንጀል የዋስትና መብት የማያስከለክለው፣ ምርመራ እየተካሄደበት ከሆነ መለቀቁ በማስረጃ ማሰባሰቡ ሂደት ላይ እንቅፋት የማይፈጥር፣ ቢለቀቅ ግዴታውን አክብሮ የሚቀርብ መሆኑን፣ መለቀቁ ለሕዝብ ፀጥታና ሠላም አስጊ አለመሆኑና ሌላ ወንጀል የማይፈጽም መሆኑን በማገናዘብ ሊሆን ይገባል፡፡

የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 63 የተያዘ ሰው የተከሰሰበት ወንጀል የሞት ቅጣትን ወይም 15 ዓመት ወይም በላይ የሆነ ጽኑ እሥራት የማያስቀጣው ከሆነና ወንጀል የተፈፀመበት ሰው በደረሰበት ጉዳት የማይሞት የሆነ እንደሆነ ፍ/ቤት የዋስትና ወረቀት አስፈርሞ ሊለቀው እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

በዋስትና ለመለቀቅ በሚቀርብ ማመልከቻ ላይ ፍ/ቤት ቶሎ ውሣኔ መሰጠት እንዳለበት የሚደነግገው ደግሞ የወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 66 ነው፡፡ በዚህ ሕግ መሠረት ፍ/ቤቱ ማመልከቻው በደረሰው 48 ሰዓት ውስጥ ውሣኔ መስጠት ያለበት መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን ከውሣኔው በፊት የዓ/ሕጉን ወይም የመርማሪውን ሃሳብና ትችት እንደሚጠይቅ ያስቀምጣል፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች ግን ይህ ሕግ ብዙ ጊዜ ሲተገበር አይታይም፡፡ በዋስትና ማመልከቻው ላይ ሃሳብ እንዲሰጥ የሚጠየቅ ዓ/ሕግ የምርመራ መዝገቡ በእጁ ስለሌለ የምርመራ መዝገቡን ከፖ/ሊስ ወስጄና ተመልክቼ አስተያየቴን ለማቅረብ ጊዜ ያስፈልገኛል ይላል፡፡ ፍ/ቤቱም ማመልከቻውን ከዓ/ሕግ አስተያየትና ከምርመራ መዝገቡ ጋር መርምሮ በተሰጠው የ48 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ለመስጠት በተግባር ችግር አለ

ይላል የዋስትና ጉዳዮችን ለብቻው የሚያዩ ችሎቶች ባለመኖራቸው ዳኞች የጊዜ ገደቡን አክብረው ውሣኔ ለመስጠት ሲቸገሩ ይታያል፡፡

የዋስትና መብት ጥያቄ መሠረታዊ ከመሆኑ አንፃር ሕጉ ሊተገበር ይገባል፡፡ ክስ ለፍ/ቤት በቀረበበት ጉዳይ ከሆነ ዓ/ሕግ የምርመራ መዝገቡን አይቶ ክስ የሚያዘጋጅ እንደመሆኑ ከሕጉ ከተቀመጠው ጊዜ በላይ ጉዳዩን የሚያራዝም የተጨማሪ ጊዜ ሊጠይቅና ሊፈቀድለት የሚገባ አይደለም፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ውስብስብ ሁኔታዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ዳኞችና ዓ/ሕጐች ፍትህ እንዳይጓደል በጥንቃቄ ሊሰሩ ይገባል፡፡ ክስ በፍ/ቤት ያልተመሠረተበት ጉዳይ ከሆነም መርማሪው ምርመራ መዝገቡ በእጁ ያለ/የነበረ እንደመሆኑ ወዲያውኑ አስተያየቱን ለመስጠት ይችገራል ሊባል አይችልም፡፡ ፍ/ቤቶችም ቢሆኑ የዋስትና ማመልከቻ ከሌሎች ጉዳዮች በተለየ ሁኔታ በአጭር ጊዜ እንዲወስኑ ሕግ የሚጠይቅ በመሆኑ ቅድሚያ ሰጥተው ሊወስኑ ይገባል፡፡

ሌላው በዋስትና ዙሪያ ትኩረት የሚሻው በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 ሥር የተደነገገው ነው በዚህ ሕግ መሠረት ዋስትና የጠየቀን ተጠርጣሪ ማመልከቻ መቀበል የማይቻለው፡-

ሀ/ በዋስትና ወረቀቱ የተመለከቱትን ግዴታዎች የማይፈፀም ነው ተብሎ ሲገመት፤

ለ/ ሌላ ወንጀል ይፈጽም ይሆናል ተብሎ የሚገመት ሲሆን፤

ሐ/ ማስረጃ ሊያጠፋ ይችላል ተብሎ ሲታሰብ ነው፡፡

ተጠርጣሪው የተከሰሰበት ወንጀል ዋስትና የማይከለከል ቢሆንም ከላይ የተጠቀሱትን የማያሟላ ተጠርጣሪ የዋስ መብቱን ሊያጣ ይችላል፡፡ በዋስትና ወረቀት የሚገለፀው ዋነኛው ግዴታ በቀጠሮ ቀን ያለመቅረት ነው፡፡ ተከሳሹ ተመልሶ ወደ ፍ/ቤት የማይመጣ ነው ተብሎ ከተገመተ አይለቀቅም፡፡ ህብረተሰብን በተጠርጣሪው ሊፈፀም ይችላል ከሚባል ተጨማሪ ወንጀል ለመጠበቅ ሲባልም ዋስትና ሊከላከል ይችላል፡፡ ሌላው ተጠርጣሪው ከዓ/ሕግ ማስረጃዎች ጋር ካለው ቀረቤታም ይሁን በሌላ ምክንያት

ማስረጃ ያጠፋል፣ ምስክሮች ሊያባብል ይችላል የሚል ግምት ካለም የዋስትና መብቱ ተጠቃሚ ላይሆን ይችላል ማለት ነው። በዚህ የሕግ አንቀጽ ሥር ከ ሀ-ሐ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ለመቀበል ሕጉ ጥያቄው የቀረበለት ፍ/ቤት ግምት ብቻ በቂ መሆኑን ያሳያል "ግዴታዎቹን የሚፈጽም የማይመስል" የሚለው ሐረግ ግምትን ያመለክታል። ይህ ማለት ግን ፍ/ቤት ከተባለው ግምት ላይ ለመድረስ ምንም መነሻ ሳይኖረው በዘፈቀደ የሚወሰነው ነው ማለት አይደለም። ለምሣሌ ያህል አንድ ተጠርጣሪ የዋስ መብቱ እንዲከበርለት ለፍ/ቤቱ ሲያመለክት ዓ/ሕጉ ወይም መርማሪው ተጠርጣሪው ተደብቆ ከሀገር ሊወጣ ሲል መያዙን ቢያረጋግጥና በዋስትና መለቀቁን ቢቃወም ፍ/ቤቱ ይህ ተጠርጣሪ/ተከሳሽ ቢለቀቅ አይመለስም ብሎ ለመገመት በቂ መነሻ ምክንያት አለው ማለት ይቻል ይሆናል።

አንዳንድ ጊዜ ተከሳሹ ዋስትና የተነፈገበት ምክንያት ከተለወጠ በኋላም ያላግባብ የሚታሰርበት አጋጣሚ አለ። በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 67/ሐ/ ሥር ማስረጃ ያጠፋል፣ ምስክር ያባብላል ተብሎ የታሰረ ተከሳሽ ማስረጃዎቹ ተሰብስበው ካለቁ በኋላ እሥሩ ሊቀጥል የሚገባበት ምክንያት የለም።

ተጠርጣሪ/ ተከሳሽ ያቀረበው በዋስ የመለቀቅ ማመልከቻ ተቀባይነት ካገኘ ተከሳሹ ዋስ እንዲጠራ ወይም ገንዘብ እንዲያስይዝ ይታዘዛል (የወ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ. 68)። ነገር ግን የዋስትና ልክን በመወሰን ረገድ ለተመሳሳይ ጉዳዮች በተለያዩ ችሎቶች/ዳኞች ዘንድ ያለው ልዩነት ከፍተኛ ነው። ብዙ ጊዜ እንደአብነት የሚጠቀሰው በቀድሞው የወ/መ/ሕ/ቁ. 526 ሥር በቸልተኝነት ሰው መግደል ለሚከሰሱ ሰዎች የሚጠየቀው የዋስትና ገንዘብ መጠን ነው። አንዱ ችሎት ከብር 500 የማይበልጥ ዋስትና ሲጠይቅ በተመሳሳይ ጉዳይ ሌላ ችሎት ብር 5 ሺ ሲጠይቅ ማየት በጣም የተለመደ ነበር። በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ሥ/ቁ. 69 ሥር ፍ/ቤት የዋስትና ገንዘብ መጠንን በመሰለው እንደሚወስን ቢደነግግም የወንጀሉን ከባድነት፣ ተከሳሹ ከቀጠሮ የማይቀር መሆኑን የተከሳሹንና የዋሱን ሀብት መጠን፣ ሲለቀቅ ያለውን አደጋ (በህዝብ ፀጥታ ላይ) ማገናዘብ እንደሚገባም ሠፍሯል።

ለአንድ ተከሳሽ የዋስትና ወረቀት ፈርሞ ዋስ የሆነ ሰው ተከሳሹ በየቀጠሮው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የማድረግ ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡

የዋስትና ግዴታ የሚገባ ሰው ይህ ግዴታው ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ በፍርድ ቤት ይወሰናል፡፡ ይህ በሥነ ሥርዓት ሕጉ የሠፈረ ቢሆንም (ቁ. 71) ብዙ ጊዜ ፍርድ ቤቶች ሲጠቀሙበት አይታይም፡፡ የዋስትና ወረቀት ፈርሞ ግዴታ የገባ ሰው ፍርድ ቤት ግዴታው የሚቆይበትን ጊዜ ካልወሰነ ጉዳዩ ዕልባት እስኪያገኝ ድረስ ይቆያል፡፡ ነገር ግን ተጠርጣሪ/ ተከሳሽ በዋስ ከተለቀቀ በኋላ እንደገና ከተያዘ ወይም ዋሱ የዋስትና ግዴታውን ፍርድ ቤት ቀርቦ ካወረደ ጉዳዩ ከማለቁ በፊትም ግዴታው ቀሪ ሊሆን ይችላል፡፡

በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 71/2/ መሠረት የዋስትናው ግዴታ የሚቆይበትን ጊዜ የመወሰን ልምድ ባለመኖሩ አንዳንዴ ችግር ሊከሰት ይችላል፡፡ ይህን ለማሳየት በሽግግሩ ዘመን የተፈጠረን ሁኔታ መጥቀሱ ጠቃሚ ነው፡፡ በአዋጅ ቁ. 22/84 የተቋቋመው የልዩ ዓ/ሕግ ጽ/ቤት በሥልጣኑ ሥር የሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮችን በሚመረምርበት ወቅት በወንጀል የሚጠረጠሩ ሰዎችን የመያዝ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በዚህ ሁኔታ የታሰሩ ሰዎች በፍርድ ቤት የአካል ነፃ ማውጣት አቤቱታዎችን ሲያቀርቡ ዓ/ሕጉ ግለሰቦቹ የማይፈቱበትን ምክንያት ካላስረዳ ፍ/ቤቶች በዋስ በርካታ ሰዎች እንዲፈቱ አድርገዋል፡፡ ከእነዚህ ሰዎች ውስጥ ቁጥራቸው ቀላል ያልነበሩ ዓ/ሕግ ክስ ሳይመሰረትባቸው ለዓመታት የቆዩ ወይም ጭራሹንም ክስ ያልተመሰረተባቸው ናቸው፡፡ ለእነዚህ ሰዎች የዋስትና ወረቀት ፈርመው ግዴታ የገቡ ዋሶች የዋስትና ግዴታቸው የሚቆይበት ጊዜ ባለመወሰኑ በተለይ ንብረታቸውን ለዋስትናው ያስያዙ፣ ሰዎች ዋስ ከሆነ ከዓመታት በኋላ እንኳን ንብረታቸውን ለመሸጥ ወይም በሌላ ሁኔታ ለማስተላለፍ የተቸገሩበት ሁኔታ ነበር፡፡

ስለሆነም ፍ/ቤት በተለይ ከክስ በፊት የዋስ መብታቸውን ለሚጠብቅላቸው ተጠርጣሪዎች የዋሶቹን የግዴታ ጊዜ በመወሰን የዋሶቹ የግዴታ ጊዜ ያላግባብ እንዳይራዘም ስለሚያደርግ የወንጀሉን ከባድነትና ነባራዊውን ሁኔታ በማገናዘብ ሕጉን መተግበሩ ጠቃሚ ነው፡፡

የዋስትና ማመልከቻው ተቀባይነት ያላገኘ ተጠርጣሪ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በሀያ ቀናት ውስጥ ይግባኝ ማመልከቻውን ማቅረብ እንደሚችል የተደነገገ ሲሆን (በቁ. 75) ይህን አንቀጽ አስመልክቶ የሚነሳው ጥያቄ ይግባኝ ለማለት የተፈቀደው ለተከሳሽ/ ተጠሪጣሪ ብቻ ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡ የዋስ መብት ጠይቆ ሊከለከል የሚችል ተከሳሽ/ ተጠርጣሪ በመሆኑ በዚህ ረገድ ተከሳሽ ያለውን መብት ለማሳየት ሕጉ በዚህ መልክ የተቀረፀ እንጂ የዋስ መብት በማይፈቅድ ወንጀል የተከሰሰን ሰው በፍ/ቤት በዋስ ቢለቀቅ ዓ/ሕግ ይግባኝ እንዳይጠይቅ የሚከለክለው አይደለም፡፡

ፍ/ቤት በዋስ የለቀቀውን ሰው መልሶ ማሰር ወይም ሌላ ዋስ እንዲጠራ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህ የሚከሰተው በበርካታ ምክንያቶች ነው፡፡ ዋሱ ቢሞት፣ ከሀገር ቢጠፋ፣ ወይም ግዴታውን ሊወጣ የማይችል መሆኑ ሲታወቅ ወዘተ...

ተከሳሽ ዋስ ጠርቶ ከእስር ከተለቀቀ በኋላ በቀጠሮው ቀን ባይቀርብ እንዲያዝ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ ዋሱም የዋስትና ግዴታ የገባበትን የገንዘብ መጠን ለመንግሥት ገቢ የማያደርግበት ምክንያት ካለው ቀርቦ እንዲያስረዳ ይጠየቃል፡፡ ካላስረዳ ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርግ ይታዘዛል (ቁ. 76)፡፡ ከእዚህ መገንዘብ የሚቻለው ዋሱ ግዴታ የገባበትን ገንዘብ ከመክፈል ያለፈ ሌላ ተጠያቂነት እንደሌለበት ነው፡፡ በሕጉ ከተመለከተው ውጭ ዋሱን ተከሳሹን ይዘህ ቅረብ ማለትም ሆነ ዋሶችም የግዴታቸውን ወሰን ባለመረዳት ፍ/ቤት ቀርበው ተከሳሹን ይዘው ለመቅረብ እንዲችሉ ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጣቸው መጠየቅ ተገቢ አይደለም፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

1. አንድ በወንጀል የተጠረጠረ ሰው የዋስትና ጥያቄ ቢያቀርብ በዋስትና እንዲለቀቅ የዋስትና ግዴታውን አያከብርም ብሎ ለመገመት መነሻዎቹ ምንድናቸው?

2. የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ .75 ዐቃቤ ሕግ ይግባኝ እንዳይጠይቅ ይከለክላል ወይ?

3. የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 63 ላይ የተጠቀሰውና ዋስትና የሚያስከለክለው ወንጀል መነሻ ቅጣቱ 15 ዓመት የሆነው ነው ወይንስ መነሻ ቅጣቱ ዝቅተኛም ቢሆን ቅጣቱ 15 ዓመት የሚደርሰው ሁሉ?

4. በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 63 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች በአንድ ላየ መሙዋላት አለባቸው ወይስ በተናጠል(cumulative or alternative requirements)?

5. ዋስትናን ለማስተናገድ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 64/2 መሰረት የግድ ጥያቄው በጽኑፍ መቅረብ የለበትም ወይ?

6. በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 63/2 መሰረት በማንኛውም ጊዜ እራሱ ተከሳሹ ከሚያቀርበው ዋስትና በተጨማሪ ለራሱ የዋስትና ግዴታ ሁል ጊዜ መፈረም አለበት ወይ?

2. የጸረ ሙስና ልዩ ሥነ ሥርዓት ሕግ

የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

ይህንን ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኃላ ሰልጣኞች፡-

- **የጸረ ሙስና የተለየ ሥነ ሥረዓት ምን እንደሆነ ያብራራሉ፤**
- **ለሙስና የተለየ ሥርአዓት ያስፈለገበትን ምክንያት ያስረዳሉ፤**
- **የጸረ ሙስና ልዩ ሥነ ሥርዓት ከመደበኛው ሥርዓት የሚለይባቸውን መንገዶች ይገልጻሉ፡፡**

የወንጀል ምርመራ፣ ክስ አመራር፣አካሄድና ዋስትናን በሚመለከት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርአት መጽሐፍ ከተመለከተው ውጭ አንዳንድ በባሕሪያቸውና አፈፃፀማቸው ለየት ይላሉ የሚባሉ ወንጀሎችን የምርመራ የማስረጃ አሰባሰበና ክስ አቀራረብን የሚደነግጉ የሥነ ሥርአት ድንግጌዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ በአዋጅ ቁጥር 434/97 (እንደተሻሻለው) የተመለከተው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርአትና የማስረጃ ሕግ ነው፡፡ በዚህ ክፍል እንመለከተዋለን፡፡

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 7 ላይ የሙስና ወንጀሎችን ለማየት ሥልጣን የተሰጣቸው የፊዴራል ጠቅላይ ና ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ሲሆኑ በክልሎች ደግሞ የክልል ጠቅላይና ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ናቸው እንዲሁም ከሙስና ወንጀል ጋር በተያየዘ የሚነሱ የመያዝ፣ የብርበራ፣ የቀነ ቀጠሮ፣ በማረፊያ ቤት የማቆየት፣ የዋስትና የእግድ እንዲሁም ከምርመራ ጋር የተያያዙ ሌሎች ተመሣሣይ ጉዳዮች የሚታዩትም በእነዚሁ ከላይ በተጠቀሱት ፍ/ቤቶች መሆኑ በዚሁ አንቀጽ 7/4/ ላይ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም ለሥልጠናው ወደ ዝርዝር ጉዳዮች መግባት አስፈላጊ ባለመሆኑ ዋና ዋና ነጥቦችን ብቻ እናነሳለን፡፡

ዋስትና

ስለዋስትና በዚህ ጽሑፍ መጀመሪያ ክፍል ተመልክተናል፡፡ የፀረሙስና ልዩ የሥነ ሥርአትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁ. 434/97 አንቀጽ 4 በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት እንዳላቸው በመርሕ ደረጃ ያስቀምጣል፡፡ ነገር ግን በሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው ወንጀሉ ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና ሊለቀቅ እንደማይችል አንቀጽ 4/1/ ይደነግጋል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 4/2/ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 28 ከተመለከተው ጋር ተመሣሣይ ሲሆን መርማሪው አንድን በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘን ሰው የዋስትና ወረቀት አስፈርሞ ስለሚለቅበት ሁኔታ የሚዘረዝር ነው፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 5 የዋስትና መብትን በማክበር ወይም በመከልከል በሚሰጥ ውሣኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 75 ላይ በዋስትና ወረቀት ለመለቀቅ የሚቀርብን ማመልከቻ ፍ/ቤት ውድቅ ካደረገ ይግባኝ ማለት እንደሚቻል በመደንገጉና ዋስትና ከተፈቀደ የይግባኝ መብት ስለመኖሩ በግልጽ ባለመደንገጉ አንዳንድ ጊዜ በፍ/ቤቶች ጥያቄ የሚያስነሳበት አጋጣሚ ስላለ በዚህ ረገድ ይህ አንቀጽ መብቱን በግልጽ ማስቀመጡ ቢያንስ የሙስና ወንጀሎችን በሚመለከት ችግሩን ያስወግዳል፡፡

አንቀጽ 5/2/ ከወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች የተለየ አዲስ ሃሳብ የያዘ ነው፡፡ አንድ በዋስትና ለመለቀቅ አቤቱታ ያቀረበ ሰው ፍ/ቤቱ የዋስትና ጥያቄውን ከተቀበለው የሚጠበቅበት ፍ/ቤቱ ስለዋስትናው የሚጠይቀውን ግዴታ ብቻ ማሟላት ነው፡፡ ይህ ከተሟላ ወዲያውኑ ይለቀቃል ማለት ነው፡፡ በፀረሙስና ልዩ የሥነ-ሥርአት ሕጉ ግን ፍ/ቤት ተከሳሽ ወይም ተጠርጣሪው በዋስ እንዲለቀቅ ቢወስንና ተጠርጣሪው ሊያሟላ የሚገባውን ግዴታ ቢያሟላ እንኳን በውሳኔው ላይ ይግባኝ ከተባለበት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኙን መርምሮ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት አይለቀቅም የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ተግባራዊ ሳይደረግ ይቆያል ማለት ነው፡፡ ዓ/ሕጉ ወይም መርማሪው በፍ/ቤቱ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የጠየቀበት መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ከይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዋስትና

ጥያቄው ላይ ውሣኔ ለሰጠው ፍ/ቤት የማቅረብ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ ፍ/ቤቱም በውሣኔው ላይ ይህንኑ ግዴታ በመጥቀስ መርማሪው ወይም አቃቤ ሕጉ ይህን ግዴታውን ባይወጣ ተጠርጣሪው እንደሚለቀቅ ማስፈር እንዳለበት በአንቀጽ 5/3/ ሥር ተመልክቷል፡፡

አንቀጽ 6ም እንደዚሁ ከወ/ሕ/ሥ/ሥ ድንጋጌዎች ለየት ያለ ነው፡፡ በዚህ ሕግ መሰረት የዋስ መብቱ የተከበረለት ሰው የመንቀሳቀስ መብቱ በተወሰነ ደረጃ ሊገደብ ይችላል፡፡ ከተወሰኑ አካባቢዎች እንዳይወጣ ከአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ እንዳይደረስ (ማስረጃ ሊያጠፋ በሚችልባቸው ቦታዎች) በተወሰነ ጊዜ ገደብ ውስጥ የሙስና ወንጀልን ለሚያጣራ ወይም ክስ ለመመስረት ሥልጣን ለተሰጠው አካል ሪፖርት እንዲያደርግ እና ወይም ከአገር እንዳይወጣ ገደብ ሊደረግበት ይችላል፡፡

እነዚህ ድንጋጌዎች ከሙስና ወንጀሎች ከባድነትና ውስብስብነት አኳያ በአንድ በኩል የዋስትና መብት መሰረታዊነት እንዳለ ሆኖ በሌላ በኩል ግን ተጠርጣሪዎች ያላግባብ ከተጠያቂነት እንዳያመልጡ በተቻለ መጠን ለመከላከል እና ጥንቃቄ ለማድረግ ታስቦ የተደነገጉ ይመስላል፡፡

ቅድመ ክስ ዝግጅት

በፀረሙስና ልዩ የሥነ ሥርአትና የማስረጃ ሕግ ውስጥ ከሰፈሩት አንቀፆች ውስጥ ከወ/ሕ/ሥ/ሥ የሚለየው አንዱ የቅድመ ክስ ዝግጅትን የሚመለከተው ክፍል ነው፡፡

የቅድመ ክስ ዝግጅትን ማከናወን አስፈላጊ የሚሆነው የሙስና ወንጀሉን የሚያየው ፍ/ቤት ሲያምንበት መሆኑ በአንቀጽ 35 ላይ በመርሕ ደረጃ ተቀምጧል፡፡ በሙስና ወንጀል የቀረበው ክስ የመደበኛውን ሥነ ሥርአት ሕግ ተከትሎ ከተካሄደ የፍርድ ሂደቱን የሚያራዝምና የሚያወሳስብ መስሎ ከታየ የቅድመ ክስ ዝግጅት ማካሄድ ተገቢ ይሆናል፡፡ የቅድመ ክስ ዝግጅት ዓላማ ለክሱ አወሣሰን ሊረዱ የሚችሉ ጭብጦችን ለመለየት ባለጉዳዮች ጭብጦቹን እንዲረዱ እገዛ ለማድረግ የክስ ሂደቱን ለማፍጠንና ፍ/ቤቱ የክሱን አካሄድ ለመምራት እንዲያስችለው ነው (ቁ.36/1/) በዚህ ሂደት በማስረጃ

ተቀባይነት እና ከክስ ሂደቱ በፊት ውሣኔ ሊያገኙ በሚገባቸው የሕግ ጥያቄዎች ላይ ውሣኔ ይሰጣል ቁ. 36/2/፡፡

ሕጉ በዋናነት ያስፈለገው ከሙስና ወንጀሎች ባሕርይ አኳያ የፍርድ ሂደቱ እንዳይንዛዛና የበለጠ እንዳይወሣሰብ ለማድረግ ነው፡፡ በቅድመ ክስ ዝግጅት ጊዜም ፍ/ቤት ውሣኔ ሊያሳርፍባቸው የሚገቡ ነገሮችን በተመለከተ በቁ. 36/2/ ላይ ተመልክተዋል፡፡

ነገር ግን አንዳንድ ተከሳሾች በተለይም በሕግ ባለሙያ የሚደገፉት ሕጉን በተገቢው መንገድ ካለመገንዘብም ይሁን ወይም ደግሞ በሌላ ምክንያት ሂደቱ ቅድመ ክስ መሆኑ እየታወቀ በክስ ሂደቱ የሚነሱ ክርክሮችን እና ዝርዝር ነገሮችን በማንሳት ተገቢ ያልሆነ የጊዜና ጉልበት ገንዘብ መባከን ያስከትላሉ፡፡ አንድ በሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው ወንጀሉን አልፈፀምኩም ካለ ያለመፈፀሙ የሚረጋገጠው በማስረጃ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሚሆነው የክስ ሂደቱ ከተጀመረ በኋላ ነው ነገር ግን በቅድመ ክስ ዝግጅት ወቅት ድርጊቱን አልፈፀመም፤በክሱ የተዘረዘሩት ፍሬ ነገሮችና የተጠቀሰው ሕግ የተለየ ናቸው ወ.ዘ.ተ. የሚሉና በማስረጃ ሊነጥሩ የሚገባቸውን ጉዳዮች ማንሳት የቅድመ ክስ ዝግጅት አላማን የሚፃረርና ጉዳዩን የበለጠ የሚያወሳስብ ነው፡፡

ስለዚህ በዋናነት የቅድመ ክስ ዝግጅት ማካሄድ ለፍርድ ሂደቱ ፍጥነት የሚረዳ መሆኑ ሊታመንበት የሚገባ ሲሆን የቅድመ ክስ ዝግጅት ማከናወን ይገባል ከተባለም በጥንቃቄ ሊመራና ሂደቱን ለማቀላጠፍ የታሰበው የበለጠ የተንዛዛ ሁኔታን እንዳይፈጥር ሕጉን በአግባቡ መተግበር ይገባል፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ፀረ ሙስና አዋጅ ቁ.434/97 አንቀጽ 5 እና 6 ላይ የተጠቀሱት ገደቦች የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 19(6) እና 32 ይቃረናሉ ማለት ይቻላል?

2. ለዋስትና በአዋጁ ላይ የተመለከተው የ10 ዓመት መስፈረት መተረጎም ያለበት እንዴት ነው? መነሻ ቅጣቱ ዝቅተኛም ቢሆን ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ ከቻለ በቂ ነው ወይ?

3. የደንብ መተላለፍ ወንጀል ሥነ ሥርዓት

የሚጠበቁ ውጤቶች

ይህ ክፍለ ትምህርት ከተጠናቀቀ በኋላ ሠልጣኞች፦

- **የደንብ መተላለፍ ወንጀሎችን ምንነት ያስረዳሉ፣**
- **የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች የሚስተናገዱበትን የተለየ ሥነ ሥርዓት አውቀው በተግባር ይተረጉማሉ።**

የደንብ መተላለፍ ጉዳዮችም በተለየ ሥነ ሥርዓት በሕጉ መሠረት መስተናገድ አለባቸው። እነዚህ ጉዳዮች ምን ዓይነት እንደሆኑ ና መከተል የሚገባን የተለየ አሠራር ምን እንደሆነ ቀጥለን እንመለከታለን።

ከሚያስከትሉት ማኅበራዊ ቀውስ ክብደትና ቅለት አንፃር ወንጀሎችን የደንብ መተላለፉ የሆኑና ያልሆኑ ብሎ መከፋፈል በሀገሮች የተለመደ ነው። የሃገራችን የወንጀል ሕግም ወንጀሎች ከሚያስከትሉት አደጋ ክብደት ና ቅለት አንፃር በሁለት ከፍሎ ይመለከታቸዋል። እነዚህም ወንጀል ና ደንብ መተላለፍ ናቸው። በደንብ መተላለፍ ተጠያቂነት የሚኖረው ጉዳዩ በወንጀል ሕግ የማይሸፈን ሆኖ ሲገኝ ብቻ እንደሆነ በወ/ሕ/አ 736/2 ስር ተደንግጓል። ወንጀል የሚባሉት ከወ/ሕ/አ 1 እስከ 733 ስር የተደነገጉት ሲሆኑ ከወ/ሕ/አ 734 እስከ 865 የተደነገጉት ደግሞ በደንብ መተላለፍ የሚሸፈኑ ናቸው።

ደንብ መተላለፍ በራሱ በማኅበረሰቡ ተቀባይነት የሌለው ተግባር ቢሆንም ከሌሎች ወንጀሎች አንፃር ሲታይ ቀላል የሚባል ነው። ደንብ መተላለፍን ልዩ የሚያደርገው የሚያስከትለው ቅጣት ነው። በደንብ መተላለፉ የተቀጣ ሰው የሚታሠረው በመደበኛ እስር ቤት ሣይሆን ለብቻው በተዘጋጀ ማረፊያ ቤት ነው። እስራቱም ከአንድ ቀን እስከ ሦስት ወር ሊረዝም ይችላል፤ የገንዘብ መቀጫ ደግሞ ከብር አንድ እስከ ብር ሦስት መቶ ወይም በልዩ ሁኔታ እስከ ብር አምስት መቶ ብር ድረስ ሊያድግ ይችላል። እንደነገሩ ሁኔታ የማረፊያ ቤት እስራትና የገንዘብ መቀጮ ተጣምሮ ሊወሰን ይችላል።

የደንብ መተላለፍ ወንጀል መፈፀም የሚያስከትለው ተጠያቂነት ቀላል መሆኑን ከግምት በማስገባት የሥነ ሥርዓት ሕጋችን ጉዳዮች የሚስተናገዱበትን አካሄድ አጭርና ቀልጣፋ እንዲሆን የሚያደርግ ሥርዓት ዘርግቷል። የደንብ መተላለፍ ወንጀል ሥነ ሥርዓት የሚመራው በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 167 እስከ 170 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ነው።

የደንብ መተላለፍ ወንጀል ሲፈፀም ዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሣሽ በቀጥታ ለፍ/ቤት አቤቱታ በማቅረብ ተከሣሹን ማስቀረብ ይችላል። ጉዳዩ ቀላል በመሆኑ የፖሊስ ምርመራ ማጣራትም አያስፈልገውም። በሚላከው መጥሪያ የተከሣሹ ስም፣ በደንብ መተላለፍ የተፈፀመው ተግባር፣ ጊዜና ቦታ፣ የተላለፈው ሕግና የሕግ አንቀፅ ተጠቅሶ ለተከሣሹ መድረስ አለበት። የፖሊስ የምርመራ የማጣራት ካለማስፈለጉ በተጨማሪ በዐቃቤ ሕግ የሚዘጋጅ ክስም አያስፈልግም። እራሱ ፍ/ቤቱ የሚያዘጋጀው ተከሣሽን የመጥሪያ ፎርም እንደ ክስ ቁጥር ያገለግላል። ወሳኙን ሥራ የሚሠራው እራሱ ፍ/ቤቱ ነው። ጉዳዩን በቀላሉ የሚያስተናግድበትን ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ኃላፊነት የፍ/ቤቱ ነው። በዐቃቤ ሕግ ክስ ቢቀርብም ፍ/ቤቱ ራሱ ያዘጋጀውን የመጥሪያ ፎርም ብቻ ነው ሞልቶ ለተከሣሹ መላክ ያለበት። በቀጠሮ ቀን ዐቃቤ ሕግና ተከሣሽም ምስክሮች ና ሌሎች ማስረጃዎችም ካሏቸው እንዲያቀርቡ በመጥሪያ ሊገለፅላቸው ይገባል። ተከሣሹ ከካደ ወይም በቀጠሮ ቀን ከቀረ በቀጥታ ጉዳዩ መታየቱ ቀጥሎ ሂደቱ እንዲፋጠን አስቀድሞ ትኩረት ሊሠጠው ና ሊፈፀም ይገባል።

ለተበደለ ወገንም ፖሊስና ዐቃቤ ሕግ ዘንድ መሄድ ሣያስፈልገው በቀጥታ አቤቱታውን ለፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል። ይህ ፍትሕ በቀላሉ ለነብረተሰቡ እንዲደርስ የተዘጋጀ ሥርዓት በመሆኑ ሊተገበር ይገባል (accessability)። ለዚህ አተገባበር ፍ/ቤት እራሱን አዘጋጅቶ በመጠበቅ ጉዳዮቹ ያለ ምንም ውጣ ውረድ በቀላሉ ዕልባት የሚያገኙበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት።

በደንብ መተላለፍ ወንጀል የተከሰሰ ሰው ጥፋተኛነቱን ፍ/ቤት መምጣት ሣያስፈልገው በጽሑፍ አድርጐ ቀን ሞልቶበት በማመን ፈርሞ ለፍ/ቤቱ መላክ ይችላል። ተከሣሹ ለምን ፍ/ቤት አልቀረበም ሊባል አይገባም። ፍ/ቤቱ የዕምነት ቃል ማረጋገጫው ከቀረበለት ዐቃቤ ሕግ ባለበት ጉዳዩን ተመልክቶ የጥፋተኛነት ውሣኔ በመስጠት የዐቃቤ ሕግን አስተያየት ሰምቶ ቅጣት መወሰንና የፍርዱን ግልባጭ ለተከሣሹ መላክ አለበት። ፍ/ቤቱ የገንዘብ መቀጮ ከወሰነ ተከሣሹ እስከ መጨረሻው ወደ ፍ/ቤት

መምጣት ሣያስፈልገው ገንዘቡን ለፍ/ቤቱ የሚላከውን የዕምነት ቃል የሚያደርስ ና የገንዘብ መቀጮን የሚከፍለው ሰው የተለየ ውክልናም አያስፈልገውም። በተከሣሹ መወከሉን በቃል ካረጋገጠ በቂ ሊሆን ይገባል። የሕጉ ዓላማ እራሱ እጅግ በቀለለና በተፋጠነ ሁኔታ እንደዚህ ዓይነት ቀላል ጉዳዮች እንዲስተናገዱ ማድረግ ነው። ተከሣሹ እራሱ ያመነ መሆኑን በፊርማውና መታወቂያውን በመሣሠሉ መንገዶች በማረጋገጥ የተከሣሹ መቅረብ በሕጉ መሠረት ካላስፈለገ ሊቀርብ አይገባም።

ተከሣሹ እራሱ በአካል ፍ/ቤት መቅረብ የሚገደደው የማረፊያ ቤት እስር፣ የግዴታ ሥራ እንዲሠራ ወይም ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ወይም መውቀስ ፍ/ቤቱ ከፈለገ ነው። ከገንዘብ መቀጮ ውጪ ያሉ ቅጣቶች ካሉ ከመወሰናቸው በፊት ተከሣሹ አስተያየቱን እንዲሰጥ ዕድል ሊሰጠው ይገባል። ተከሣሹ በዚህ ሁኔታ መጥሪያ ደርሶት ካልቀረበ ፍ/ቤቱ ታስሮ እንዲቀርብ ከማድረግ የሚያግደው ነገር አይኖርም። እዚህ ጋር ሊተኮርበት የሚገባው ነጥብ የሕጉ ዓላማ የተለየ ሁኔታ ካላገጠመ በስተቀር ተከሣሹ ሥራ ፈቶ ፍ/ቤት በመምጣት እንዲጉላላ አለመፈለጉን ነው። ሕጉ በጣም ቀላል ጥፋት አድርጌ ለቆጠራቸው ተግባራት ሰጥፋቱ ጋር የማይመጣጠን መጉላላት በተከሣሽ ላይ መድረስ የለበትም። መደበኛውን የወንጀል ፍርድ ሂደት ተቃራኒ አካሄድ ነው መከተል የሚገባው። ጉዳዩ በተቻለ መጠን ተቀላጥፎ እልባት ሊያገኝ የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይገባል። የተንዛዛ አካሄድ ግን ሲተገበር ይስተዋላል። እንደ መደበኛ የወንጀል ፍርድ ሂደት ከፖሊስ ምርመራ ጀምሮ ሲከናወኑ ይታያል። ይህ ሕጉን ያልተከተለ ነው። ሰዎች ፍ/ቤት ካልቀረባችሁ እየተባሉ ለወጪና ለእንግልት ሊዳረጉ አይገባም።

ተከሣሹ ከፍ/ቤት በመጥሪያ መልክ የደረሰውን ክስ የማያምንበት ከሆነ ፍ/ቤት መቅረብ አለበት። ዐቃቤ ሕግም ተከሣሽም ምስክሮች ወይም ሌላ ማስረጃ ካላቸው በቀጠሮ ቀን ማቅረብ አለባቸው። የግራ ቀኙን ምስክሮች በቃል ብቻ በመስማት ወሣኝ የሆነ ቃላቸውን ብቻ በመመዝገብ ማስረጃ የመስማት ሂደት ማብቃት አለበት። ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ወዲያው ተፈፀመ የተባለውን ተግባርና ተጣሰ የተባለውን ሕግ ጠቅሶ አጭር የቃል ፍርድ መስጠት አለበት። ሁሉ ነገር በአንድ ቀጠሮ ሊያልቅ የሚችል ነው። ከጥፋተኝነት በኋላ የሚከተለው ቅጣት ቀላል በመሆኑ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙ ማስረጃቸውን ያለበቂ ምክንያት ካላቀረቡ ቀጠሮ መለወጥ የለበትም። ሂደቱን ማፋጠን አለበት። ተከሣሹ የፍ/ቤት መጥሪያ ደርሶት ካልቀረበ በሌለበት ወዲያው ክሱን በመስማት ውሣኔ ማግኘት አለበት። የሚጣለው ቅጣት የገንዘብ ከሆነ ተከሣሹ በአካል መቅረብ

ሣያስፈልገው ክፍያውን የሚፈፅምበት ሁኔታ መመቻቸት አለት። ከገንዘብ ውጪ የሆኑ ቅጣቶች ተከሣሹ በሌለበት የሚወሰኑ ከሆነ ተከሣሹ በፍ/ቤት መጥሪያ ተጠርቶ መቅረብ አለበት። በዚህ ጊዜ ተከሣሹ የፍ/ቤቱን መጥሪያ አክብሮ የማይቀርብ ከሆነ ታስሮ እንዲቀርብ ሊደረግ ይችላል።

ቀደም ብሎ ከዐቃቤ ሕግ ክስ አመሠራረትም ጋር ተያይዞ እንደተገለፀው የወንጀል ና የደንብ መተላለፍ ጉዳዮችን መለየት ግን ቀላል አይደለም። ቀደም ብሎ በሌላ ክፍል ከተጠቀሱት የሕጉ ድንጋጌዎች በተጨማሪ በወንጀል ሕጉ የሚገኙና በተነፃፃሪነት በደንብ መተላለፍ ውስጥ የተካተቱት ከሁለቱ በየትኛው ውስጥ እንደሚወድቁ የሚያወዛግብ ተግባራትን የሚያስቀምጡ ድንጋጌዎች ይገኛሉ። ለአብነት ያክል የሚከተሉትን በተጨማሪነት በወንጀል ሕጉ የሚገኙና በተነፃፃሪነት በደንብ መተላለፍ ውስጥ የተካተቱት ከሁለቱ በየትኛው ውስጥ እንደሚወድቁ የሚያወዛግብ ተግባራትን የሚያስቀምጡ ድንጋጌዎች ይገኛሉ።

ለምሳሌ ያክል የሚከተሉትን በተጨማሪነት መዘርዘር ይቻላል። እነርሱም የወ/ሕ/አ 481 እና በሌላ ወገን የወ/ሕ/አ 808 እና 809፤ በወ/ሕ/አ 555 እና 556 ስር የተጠቀሱትን ተግባራት ለመፈፀም በወ/ሕ/አ 27/1 መሠረት ጉዳት ለማድረስ ስለታም ነገር የመወርወር ሙከራ እና በተቃራኒው የወ/ሕ/አ 823/ለ እንዲሁም የወ/ሕ/አ 665 እና በተነፃፃሪነት የወ/ሕ/አ 851/ሀ የመሳሰሉት ናቸው። አንድ ጉዳይ በአንድ አንቀጽ ስር ብቻ ሊሸፈን ከቻለ በሁለቱም በወንጀልና በደንብ መተላለፍ በአንድ ጊዜ አያስጠይቅም። የሚመሳሰሉ ድንጋጌዎች ሲያጋጥሙ በቅድሚያ የወንጀል ሕጉ በሚገባ የሚሸፍናቸው መሆኑ መረጋገጥ አለበት። ዋናው የወንጀል ሕግ የማይሸፍናቸው ከሆነ ነው ወደ ደንብ መተላለፍ ድንጋጌዎች ማምራት ያለብን። የሕጋዊነት መርህን የሚደነግጉት በወ/ሕ/አ 2/5 እና 736/3 መሠረት አንድ ድርጊት የሚያስቀጣው በወንጀል ሕግ ወይም በደንብ መተላለፍ ሕግ ከሁለቱ በአንደኛው ብቻ እንጂ በሁለቱም መሆን የለበትም። ነገር ግን በሁለቱም የሚያስጠይቅ ጉዳይ ሲያጋጥም ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ክስ ማቅረብ ይቻላል። ለምሳሌ በስለት ሰው የወጋ ግለሰብ አካል ላይ ጉዳት በማድረስ ና ለብቻው ደግሞ በደንብ መተላለፍ ወንጀል ስለት በመያዙ ብቻ ሊጠየቅ ይችላል።

በመሆኑም የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች ሕጉ ቀላል ማኅበራዊ ቀውስን ሊያስከትሉ የሚችሉ ወንጀሎች አድርጐ ነው ያስቀመጣቸው:: ጉዳዮቹ አነስተኛ ግምት በሕጉ የተሰጣቸው በመሆኑ አላስፈላጊ በሆነ ሁኔታ የመንግሥትና የተከሰሰውን ሀብትና ጉልበት ለኪሣራ መዳረግ የለባቸውም:: የሕጉን ዓላማ ተከትሎ ጉዳዮቹ በተቻለ መጠን እጅግ በአጠረ ና በተቀላጠፈ ሁኔታ የሚስተናገዱበት መንገድ መመቻቸት አለበት::

የመወያያ ነጥቦች

1. የደንብ መተላለፍ ወንጀል ምንድነው ?

2. ለደንብ መተላለፍ ጉዳዮች ሕጉ የተለየ ሥርዓት የዘረጋው ለምንድነው?

3. ለደንብ መተላለፍ የተዘረጉት የተለያዩ ሥርዓቶች ምንድናቸው? ከመደበኛው የወንጀል ፍትሕ ሂደት በምን ይለያሉ?

4. በጽሑፉ ውስጥ የተጠቀሱት የወንጀል ሕግ እና የደንብ መተላለፍ ሕግ ድንጋጌዎች በተግባር እንዴት ተተርጉመው ሥራ ላይ ሊውሉ ይገባል?

4. በወንጀል ነገር ገብተው የተገኙ ህጻናት የፍርድ ሒደት/Children in Conflict with the Law/

የሚጠበቁ ውጤቶች

- **ይህ ክፍለ ትምህርት ሲጠናቀቀ ሰልጣኞች፡-**
- **የወጣት አጥፊነት የፍትህ ሥርዓትን ምንነት ያስረዳሉ፣**
- **ለወጣት ጥፋተኞች የተለየ የፍትህ ስርዓት መዘርጋት ያስፈለገበትን ምክንያት ይገልጻሉ፡፡**
- **ለወጣት አጥፊዎች በህገ መንግስቱ እና በሐገራችን ጭምር በፀደቁት በአለም አቀፍ እና አህጉር አቀፍ የሰብአዊ መብት ሰነዶች የተደረገውን ጥበቃ ተገንዝበው ለተግባራዊነቱ በጽናት ይቆማሉ፣**
- **ለወጣት አጥፊዎች የተዘረጋውን የፍትህ ስርዓት ሂደት ይተነትናሉ፡፡**

ህጻናት በወንጀል ነገር ገብተው ሲገኙ የሚስተናገዱበት ሂደት ከአዋቂዎች የተለየ ነው፡፡ የተለየ ጥበቃ የሚደረግላቸውን ህጻናት በመለየት ይህ ልዩ ስርዓት ያስፈለገበትን ምክንያት ና ሂደቱ ምን እንደሚመስል ይዳስሳል፡፡

የወጣት አጥፊነት የፍትህ ሂደት የሚባለው ህጻናት ወንጀል ፈጽመው ሲገኙ የምንከተለው ስርዓት ነው /Juvenile delinquency/፡፡ አዋቂዎች ወንጀል ፈጸሙ ሲባል ከምንከተው መደበኛ አሰራር የተለየ ነው፡፡ ህጻን ማነው የሚለው በቅድሚያ መታወቅ አለበት፡፡

ህጻን ማለት ኢትዮጵያ በአፀደቀቻቸው የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን /ህመኮ/ አንቀፅ 1፣ የአፍሪካ ህጻናት መብቶች እና ደህንነት ቻርተር /አህመደቻ/አንቀፅ 2፣ እና በኢትዮጵያ የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 215 መሰረት እድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ነው፡፡ የህጻናት እድሜ ገና ለጋ በመሆኑ አካል ና አስተሳሰባቸው ስለማይጎለብት በቀላሉ ተታለው ወይም ተገደው ለጉልበት ብዝበዛ ለወሲብ ጥቃትና ለመሳሰሉ ችግሮች ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡ በዚህ ብቻ ሣይወሰን በአስተዳደጋቸው በስነምግባር ካልታነጹ፣ትምህርት እንዲያገኙ ከልተደረገ እና እንክብካቤ ካልተደረገላቸው ወደ ወንጀል ተግባር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ለሁለመና እድገታቸው የአዋቂዎችን ድጋፍና እገዛ ይሻሉ፡፡ ይህ ከተነፈጋቸው ለከፍተኛ አደጋ ይጋለጣሉ፡፡ ለዚህ ነው ለጥቃት ከሚጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች /vulnerable groups/ ተርታ የሚመደቡት፡፡ ትውልድ እንዲቀጥል የዛሬ አበቦች የነገ ፍሬዎች በሚለው የአገራችን ብሒል ለሚታወቁት ህጻናት የተለየ እንክብካቤ እንደሚያስፈልግ አያከራክርም፡፡ ለዚህ ነዉ የህመኮም ከአሜሪካ እና ከሶማሊያ ውጪ በሁሉም የአለም ሀገራት የፀደቀ ነው፡፡ ይህ በአለም ላይ በህጻናት ጉዳይ ላይ ያለውን የአስተሳሰብ አንድነት ማረጋገጫ ነው፡

ህጻናት ገና በአካልም ሆነ በአእምሮ ያልበሰሉ በመሆናቸው ወደ ወንጀል ውስጥ ገብተው ከተገኙ መታየት ያለበት በዋነኛነት ለዚህ ችግር የዳረጋቸው ምክንያት ነው፡፡ አጥፍተው ሲገኙ አላማው እነሱን መቅጣት ሣይሆን በቀላሉ ሊታረሙ የሚችሉበት የእድሜ ሁኔታ ላይ ስለሚገኙ የወደፊት ህይወታቸው ፈር የሚይዝበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው፡፡ የፍትህ አካላት ሚና መሆን ያለበት እንደ ሐኪም ችግራቸውን ተረድተው መፍትሔ ማፈላለግ ነው፡፡ ለዚህም ተግባር ፍ/ቤቶች የህጻናቱን ችግር ለመገንዘብ የስነ ልቦና እና የማህበራዊ ሣይንስ ባለሙያ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በአዲስ አበባ ፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያለው ባለሞያዎችን በህጻናት ጉዳይ የማሳተፍ አሰራር በሁሉም ፍ/ቤቶች ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡

ለወንጀል ተግባር ህጻን ማለት /criminal majority/ እና ለፍትሐብሔር ተግባር ህጻን ማለት / civil majority/ የተለያየ ነው፡፡ ለወንጀል ጊዜ የተጠያቂነቱ እድሜ መነሻ እንደ ሃገሩ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል፡፡ የወንጀል ተጠያቂነት እድሜ ከፍትሐብሔር ዝቅ ያለ ነው፡፡ በአገራችን ህጻናት ዝቅተኛ የወንጀል ተጠያቂነት እድሜ በወ/ህ/አ 53

መሰረት 9 ዓመት ነው፡፡ ወጣት አጥፊዎች ተብለው የተለየ ጥበቃ የሚያገኙት እድሜያቸው 9-15 ዓመት የሚሆኑ ህጻናት ናቸው፡፡ በዚህ ፅሑፍ ውስጥም ህጻናት ተብለው የሚጠቀሱትም እነዚሁ ክፍሎች ብቻ ናቸው፡፡ 15ኛ ዓመት ልደቱን ካከበረ ህጻን በመሰረቱ እንደ አዋቂ ነው ለወንጀል ህግ ተግባር የሚቆጠረው፡፡ በወ/ህ/ዓ 56 መሰረት እድሜያቸው 15-18 ለሆኑት ህጻናት ጥበቃ የሚያደረገው ከጥፋተኝነት ውሣኔ በኋላ በቅጣት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ የጥበቃው አድማስ ጠባብ ነው፡፡ ሁሉም ህጻናት ሊከተቱ ይገባል የሚል ተቃውሞ በህጻናት ዙሪያ ከሚሰሩ ድርጅቶች ይደመጣል፡፡ ወጣት አጥፊነትን የፍትህ ስርዓት ሂደት የሚገዙት ድንጋጌዎች በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 171-180 ያሉት ናቸው፡፡

ህጻናት በህገ መንግስቱ፣ ህመኮ እና አህመድቻ የተለየ ጥበቃ የሚደረግላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ በእድሜያቸው ገና ያልበሰሉ በቀላሉ ሊታረሙ የሚችሉ ናቸው፡፡ የአገር ሃብት እንደሆኑት ሁሉ በአግባቡ የሚታረሙበት ሁኔታ ካልተመቻቸ የአገር እዳ ነው የሚሆኑት/children as an asset and liability/፡፡ ለዚህ ነው በህግ መሰረት የተለየ ጥበቃ የሚደረግላቸው፡፡

ህጻናት በወንጀል ነገር ገብተው ከተገኙ ፖሊስ፣ዓ/ህግ፣ወላጅ፣ ሞግዚት ወይም የተበደለ ወገን ህጻኑን በጥበቃ ወደ ፍ/ቤት መውሰድ አለበት፡፡ በተበዳይ አቤቱታ የሚቀርብ ከሆኑ ተበዳዩ አቤቱታ በቅድሚያ ማቅረብ አለበት፡፡ ፖሊስ በፍርድ ቤት የሚሰጠውን ትእዛዝ ሣይቀበል ምርመራውን ማከናወን አይችልም፡፡ ምርመራን ማጣራት የሚኖርበት ፍ/ቤቱ በሚሰጠው መመሪያ ላይ በመመስረት ነው፡፡

በጉዳዩ ዓ/ህግ የሚገባው ህጻኑ ከ10 ዓመት በላይ በሆነ ፅኑ እሥራት ወይም በሞት በሚያስቀጣ ወንጀል ከተከሰሰ ነው፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ጉዳዬች ዓ/ህግ ክስ አዘጋጅቶ ማቅረብ አለበት፡፡ በሌሎች ጉዳዩች ግን ዓ/ህግ ክስ ማቅረብ አይችልም፡፡ ዓ/ህግ ክሱን አዘጋጅቶ ካቀረበ በኋላ ጉዳዩን መከታተል ስለመቻል አለመቻሉ ህጉ ላይ የተቀመጠው በከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚቀርቡ ጉዳዩች ላይ ብቻ ነው፡፡ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 176 መሰረት ዐ/ህግ በከፍተኛ ፍ/ቤት በሚታዩ ጉዳዮች ላይ መገኘት አለበት፡፡ ህጉ ከወጣ በኃላ የፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን ለውጦችም አሉ፡፡ ስለሌሎች ፍ/ቤቶች የተገለፀ ነገር

የለም:: ዐ/ህግ ክሱን ካቀረበ በኃላ መከታተል ስለ መቻሉ ሁለት ዓይነት አተረጓጎም አለ፡፡ አንደኛው ዓ/ህግ ክሱን ካቀረበ በኋላ በችሎት ጉዳዩን የመከታተል መብት የለውም የሚለው ነው፡፡ ሌላኛው ዓ/ህግ ክሱን ካዘጋጀ ሊከታተል ይገባል፡፡ ካለዚያ የማይከታተለውን ክስ ማዘጋጀቱ ትርጉም የለውም የሚለው ነው፡፡ አሳማኝ የሚመስለው የኋላኛው አተረጓጎም ነው፡፡ አዲስ አበባ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አሁን ባለው አሰራር በህግ በታዘዘ ጊዜ ዐ/ህግ ክስ አዘጋጅቶ ቢያቀርብም ክሱን በችሎት ተገኝቶ መከታተል አይፈቀድለትም፡፡

የህጻን ወላጆች፣ሞግዚት፣ አሣዳሪ ወይም ሌላ ቤተዘመድ ካልቀረበ ወይም ከ10 ዓመት በላይ ዕኑ እሥራት ወይም በሞት በሚያስቀጣ ወንጀል ህጻኑ ከተከሰሰ ፍ/ቤቱ የግድ ለህጻኑ ጠበቃ እንዲቆም ማድረግ አለበት፡፡

ጉዳዩ ክስ ሣይሰማ ሊቋረጥ የሚችለበት ሁኔታ እንዳለ በህጉ ላይ በግልፅ የተመለከተ ነገር የለም፡፡ ህጻኑ እንደቀረበ ፍ/ቤቱ ያመጣውን ወገን የወንጀሉን እና የምስክሮቹን ዝርዝር ተቀብሎ መመዝገብ ይበጠቅበታል፡፡ በመደበኛ ሁኔታ የሚስተናገድ ሁኔታ ቢሆን ኖሮ ዐ/ህግ በቂ ማስረጃ የለም በማለት ክሱን ሊዘጋ ይችል ነበር፡፡ ፍ/ቤት ጉዳዩን በሚመለከትበት ጊዜ ወደ ክስ መስማት ለመሔድ የሚያስችል በቂ ማስረጃ ያለመኖርን ከፖሊስ ምርመራ ማጣራት በኋላ ካረጋገጠ በኋላ ወደ ክስ መስማት ሒደት መሄድ ያለበት አይመስልም፡፡ ለማንኛውም ሰው የተጠበቀ መብት ለህጻናት ሊነፈግ አይገባም፡፡ በተበዳይ አቤቱታ የሚቀርብ ክስ ከሆነ እና ተበዳይ ክሱን ካልፈለገ ክሱን መቋረጥ እንዳለበት ግልፅ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ላሉ ህጋዊ ምክንያቶች ፍ/ቤቱ ክሱን ሣያሰማ ጉዳዩን ሊያቋርጥ ስለመቻሉ በህጉ ላይ በግልፅ የተመለከተ ነገር አለመኖሩ የህጻኑን መብት ሊያጣብብ ይችላል፡፡

ህጻኑ ፍ/ቤት ከቀረበ በኋላ መዝገቡ መቀጠር ካለበት ህጻኑን ሊረከብ ለሚችል ወላጅ ወይም ዘመድ ወይም ተቋም መሰጠት አለበት፡፡ ህጻኑን የሚረከብ ዘመድ ህጻኑን በቀጠሮ ቀን እንዲያቀርብ በፍ/ቤት በሚወሰነው የገንዘብ መጠን ቢያንስ በቀጠሮ ቀን ለማቅረብ ዋስትና ሊፈርም ይገባል፡፡ ዝም ብሎ ህጻኑን አቀርበለሁ ብሎ ማስፈረም ለአፈጻጸም ሊያስቸገር ይችላል፡፡ ህጻኑን ባለማቅረብ ሊከተል የሚገባ የተጠያቂነት

መንፈስ ሊኖር ይገባል። በተግባር ግን ይህ ሲደረግ አይስተዋልም። ነገር ግን ተረካቢም እንዳይጠፋ ለራስ የሚፈረም ዋስትናም ቢሆን መጠኑ ለይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል። አለዚያ ህጻናት ጉዳዩ እስኪታይ በቀላሉ ለእስር ሊዳረጉ ይችላሉ።

የችሎቱ አካሒድ መደበኛ የፍ/ቤት ሒደትን የማይከተል መሆን አለበት። በሒደቱ ላይ ህጻኑ ሊሰማው የማይገባዉ ነገር ካለ በችሎት እንዲወጣ መደረግ አለበት። በችሎቱ ውስጥ ዓ/ህግ ሊገኝ የሚችልበት ልዩ አጋጣሚ ከላይ ከተገለፀው ውጪ መገኘት የሚችሉት ምስክሮች፣ልዩ አዋቂዎች፣ወላጆች፣ሞግዚት ወይም የበጎ አድራጊዎች ድርጅቶች አባላት ናቸው። ጉዳዩ በዝግ ችሎት የሚስተናገድ ነው።

ክሱ ሲሰማ መቃወሚያ ማቅረብ ስለመቻል በህጉ በግልፅ የተደገገ ነገር ባይኖርም ይህንን መብት ህጻኑ ሊነፈግ አይገባም። መነሣት ያለበት ነጥብ ካለ መቅረቡ ተገቢ ነው። ህጻናትን በተመለከተ የሚሰጥ ፍርድ የተለየ ባህሪ ተብሎ ሊጠቀስ የሚገባው ጉዳይ ታይቶ የተሰጠ የመጨረሻ የሚፈፀም ውሣኔ ወይም ትእዛዝ ቢኖርም ሊሻሻል መቻሉ ነው። ፍ/ቤቱ በራሱ አስተያየት ወይም የህጻኑ ሐላፊ ወይም አደራ የተቀበለ ሰው ወይም ድርጅት ጥያቄ የተሰጡ ውሣኔዎች እና ትእዛዞች እንደተፈለገ ሊሻሻሉ ወይም ሊለወጡ ይችላሉ። ይህም የሁኔታዎችን ተለዋዋጭነት ከግምት በማስገባት ለህጻኑ ሊጠቅም የሚችል ማንኛውም ክስተት እያገናዘቡ ለህጻኑ ጥቅም የሚያግዙ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችል ነው። የህጻናት የፍትህ ሥርዓት የተለየ የሚያደርገው ሌላው አሰራር ጉዳዩ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 160 መሰረት ህጻኑ በሌለበት ሊስተናገድ አለመቻሉ ነው።

የሚሻሻለው የወንጀል ህግ ስነ ስርዓት የህጻናት ወንጀል ፍትህ ስርዓት ላይ እያጋጠሙ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት በሚያስችል መንገድ ሊሻሻል ይገባል። በመሆኑም ህጻናት በህገ መንግሥቱ፣በአለም አቀፍ፣ አህጉር አቀፍ እና አገር አቀፍ ህጎች ውስጥ የተደረገላቸውን ጥበቃ በመገንዘብ ሁሉም የሚመለከታቸው የፍትህ አካላት ለተግባራዊነቱ በጽናት መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

የመወያያ ነጥቦች

1. የወጣት አጥፊዎች የፍትህ ሥርዓት ምንድነው?

2. ህጻናት የወንጀል ነገር ገብተው ሲገኙ የተለየ ጥበቃ የሚደረግላቸው ለምንድ ነው?

3. በህገ መንግስቱ በህመኮ እና በአሕመድቻ ለወጣት አጥፊዎች ጥበቃ የሚሰጡት ድንጋጌዎች በሀገራችን አሁን ባለው ሁኔታ በወንጀል ህጉ ስነስርዓት አተገባበር ላይ እየተንጸባረቁ ነው ወይ?

4. እድሜያቸው ከ15 እስከ 18 አመት የሆኑ ህጻናትን እድሜያቸው ከ9 እስከ 15 ዓመት እንደሆኑ ህጻናት በተመሣሣይ ሁኔታ ቢስተናገዱ ምን ጥቅምና ጉዳት ይኖረዋል?

5. ከፍትህ አካላት በህገ መንግሥቱና በአለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ሰነዶች የተደነገጉ የህጻናት መብቶችን ለማክበር ና ለማስከበር ምን ይጠበቃል?

6. የወጣት ጥፋተኞች የፍትህ ሂደት እንዴት ይተገበራል?

7. ፍ/ቤት ፖሊስን የምርመራ መዝገብ ተመልክቶ ከክስ መሰማት በፊት መዝገቡን በህግ ለዓ/ህግ በተሰጡት ስልጣኖች መሰረት ለመዝጋት በህግ ስልጣን ተሰጥቶታል ወይ?

8. ህጻኑን ለመረከብ የሚጠይቅ ሰው የዋስትና ግዴታ መግባት አለበት ወይ?

9. ዓ/ህግ ህጻናትን በተመለከተ በወረዳ ወይም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሚስተናገዱ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጡ የወንጀል ጉዳዮች ክስ ካዘጋጀ በኃላ ችሎት ተገኝቶ መከታተል ሊፈቀድለት ይገባል ወይ? በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 176 ስር

ለከፍተኛ ፍ/ቤት ለሚቀርቡ የወንጀል ጉዳዮች ዐ/ህግ በችሎት ተገኝቶ እንዲከታተል ከተደነገገው አንጻር እነዴት ያዩታል?

5. ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክስን መስማት

የሚጠበቁ ውጤቶች

ሰልጣኞች ከስልጠናው ማብቂያ ላይ፡-

- ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ጉዳይ ሊታይ የሚችልበትን መንገድ ያስረዳሉ፤
- ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠ ፍርድ ጉዳን ባየው ፍ/ቤት ተሸሮ እንደ አዲስ ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ ይዘረዝራሉ፡፡

በመርህ ደረጃ ክስ መሠማት ያለበት ተከሳሽ ባለበት ነው፡፡ በወንጀል ተጠርጥሮ የተከሰሰ ሰው ፍርድ ቤት ቀርቦ ክሱ ደርሶትና ተረድቶት የመሰማት ሕገ መንግሥታዊ መብት እንዳለው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንሥግሥት አንቀጽ 20 ደንግጓል፡፡ ይህ ማለት ግን የወንጀል ክስ ሁሉ ተከሳሽ ፍርድ ቤት ካልቀረበ ታይቶ አይወሰንም ማለት አይደለም፡፡

በሕግ ተለይተው በተመለከቱ ወንጀሎች ላይ ተከሳሽ በሌለበትም ክሱን መርምሮ መወሰን ይቻላል፡፡ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ አራተኛ መድሐፍ አንቀጽ 2 ልዩ ሥነ ሥርዓት በሚለው በምዕራፍ አንድ ቁጥር 160/2/ ሥር ነገሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ተከሳሽ ካልቀረበ ወይም ለመቅረቱ በቂ ምክንያት የሚሰጥለት እንደራሴ ካልቀረበ እንዲያዝ ትዕዛዝ ፍ/ቤት እንደሚሰጥ ይደነግጋል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ መሠረት መፈፀም ካልተቻለ ተከሳሹ በሌለበት ነገሩን ለመስማት ፍ/ቤቱ እንደሚያስብበት የዚሁ ቁ. 160/3/ ያስቀምጣል፡፡ ከዚህ መርህ ሁለት ነጥቦችን እናያለን፡፡ ተከሳሽ ሲቀር የመጀመሪያው የፍ/ቤቱ ተግባር እንዲያዝ ማዘዝ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በሌለበት ጉዳዩን ለማየት ማሰብ ናቸው፡፡

አንድን የወንጀል ክስ ተከሳሽ በሌለበት መስማትና መወሰን የሚቻለው በቁ. 161/2/ መሠረት ከ12 ዓመት በማያንስ ጽኑ እሥራት የሚያሳስር ወንጀል የሠራ ወይም

በቀድሞ ወ/መ/ሕግ ቁ. 354-365 በአዲሱ የወንጀል ሕግ ቁ. 343 እስከ 354 ድረስ ያሉ ወንጀሎች ፈጽሞ ጽኑ እሥራት ወይም ከ5000 ብር በላይ በሚያስቀጣ ወንጀል የተከሰሰ ሲሆን እና እንዲሁም በውጭ ሀገር ጥገኛ ሆኖ ጥገኛ ያደረገው ሀገር አሳልፎ ያልሰጠው እንደሆነ ነው ቁ. (161/3/) ተከሳሹ በቁ. 160/2/ ካልቀረበ ወይም ለመቅረቱ በቂ ምክንያት ካልተሰጠና ወንጀሉ በቁ. 161/2/ እና /3/ የተመለከተው ከሆነ ክሱ በሌለበት እንዲሰማ ይታዘዛል። በቁ. 162 መሠረት ፍ/ቤት በጋዜጣ ማስታወቂያ ተከሳሽ እንዲጠራ የሚያዘው ነገሩ እንዲሰማ ቀጠሮ በተሰጠበት ቀን ባይቀርብ በሌለበት ጉዳይ እንዲታይ በታዘዘው መሠረት ቀጥሎ እንደሚታይ ለማስታወቅ ነው። ከጋዜጣ በተሻለ በሌላ መንገድ መጥሪያው ለተከሳሽ ሊደርስ ይችላል ከተባለም አማራጩ ለፍ/ቤት የተተወ ነው።

በተግባር የሚታየው አሠራር የተለየ ሊመስል ይችላል በቁ. 161 የተመለከቱት ሁኔታዎች በተሟሉበትም ቢሆን ፍ/ቤት የተከሳሽን ጉዳይ በሌለበት ለማየት የሚወሰነው በጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ ካደረገ በኋላ ነው ምናልባትም ይህ አሠራር የተከሳሹን መብት በተሻለ መንገድ ይጠብቅለታል ከሚል የመነጨ ይመስላል። ነገር ግን ፍ/ቤቱ ተከሳሹ የቀረው ያለበቂ ምክንያት መሆኑን ካረጋገጠ በጋዜጣ ጥሪ የሚያደርግበት አግባብ የለም።

በዚህ ሁኔታ በሌለበት ጉዳዩ ታይቶ የተፈረደበት ሰው ፍርዱ ውድቅ እንዲደረግለት ፍርዱን ባወቀ በ30 ቀን ውስጥ ለፈረደው ፍ/ቤት ማመልከት ይችላል (ቁ. 164,197,198) ማመልከቻውም ተቀባይነት የሚያገኘው ተከሳሹ ፍ/ቤት ያልቀረበው መጥሪያው ስላልደረሰው ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የቀረ መሆኑን ማስረዳት ከቻለ ብቻ ነው። ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ምንድነው የሚለውን የመወሰን ኃላፊነት የፍርድ ቤቱ ነው። ማመልከቻው ተቀባይነት አግኝቶ ፍ/ቤቱ በሌለበት የሰጠውን ውሣኔ ውድቅ ካደረገው ጉዳዩ/ ክሱ እንደገና በሌላ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት እንዲታይ ይታዘዛል ቁ. 202።

በሌለበት የተፈረደበት ፍርድ እንዲነሳለት ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ የተደረገበት ተከሳሽ ይግባኝ ማለት የሚችለው በቅጣቱ ላይ ብቻ ነው።

<u>በግል ክስ ፍርድ ቤት አለመቅረብ፡፡</u>

በግል የሚቀርቡ ክሶች ምንነት በሞጁል አንድ ስር የተካተቱ በመሆናቸው እዚህ አናነሳቸውም፡፡ በዚህ ክፍል ትኩረት የሚሹት ሁለት ነጥቦች ናቸው፡፡ በግል በሚቀርቡ ክሶች ተከሳሽ ባይቀርብ ከላይ በቁ. 162 እና 163 ሥር እንደተመለከተው በሌለበት ክሱ አይቀጥልም፡፡ ይህም በግል የሚቀርቡ ተብለው በወንጀል ሕጉ የተቀመጡት ወንጀሎች ግለሰብን እንጂ ህብረተሰቡን በቀጥታ የማይነኩ ግላዊ ባህሪይ ያላቸው በመሆናቸው ነው፡፡

በግል ክስ ተከሳሽ ባይቀርብ ፍ/ቤት ተከሳሹን እንዲያዝ ያዛል (ቁ. 166) ተከሳሹ ባይገኝ ፍ/ቤቱ ለስንት ጊዜ እንደሚያዝ ሕጉ አይመልስም ተከሳሹ ባለመገኘቱ ደግሞ መዝገቡ በእንጥልጥል ላልተወሰነ ጊዜ በቀጠሮ ማቆየትም ተገቢ አይሆንም፡፡ ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም ተከሳሹ በተገኘ ጊዜ ክሱን ማንቀሳቀስ እንደሚችል ጠቅሶ መዝገቡን መዝጋት ይገባል፡፡ ክሱ ሊንቀሳቀስ የሚችለው ግን የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜው ከማለፉ በፊት ሊሆን ይገባል፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

1. አንድ ተከሳሽ ጉዳዮ በሌለበት የሚታየው መነሻ ቅጣቱ 12 ዓመት ከሆነ ነው ወይንስ መነሻ ቅጣቱ ዝቅ ያለ ቢሆንም 12 ዓመት ድረስ ካስቀጣ ነው?

2. በሌለበት የተፈረደበት ሰው ያልነበርኩት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው ሲል ጉዳዮ ከአቅም በላይ ነው ለማለት መስፈርቱ ምንድንነው?

3. በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 202 መሰረት ጉዳዩ እንደገና መታየት ካለበት ዐ/ሕግ ስለሁኔታው በ ክሱ ላይ ገልጾ አዲስ ክስ በሌላ መዝገብ ማቅረብ አለበት ወይስ በዚያው መዝገብ ላይ ጉዳዩ በሌላ አዲስ ዳኛ/ኞች እንዲታይ መደረግ አለበት?

5. ተከሰሹ የፍ/ቤት መጥሪያ ደረሶት ቢቀር እና ታስሮ እንዳይቀርብ ቢሰወር ወይም ጉዳዩን መከታተል ከጀመረ በኃላ ሆነ ብሎ ቢሰወር በጋዜጣ እንዲቀርብ ጥሪ ማድረግ ተገቢ ነው ወይ? ፍ/ቤቱ ስለ ሁኔታው መዝግቦ ጉዳዩን ተከሳሽ በሌለበት በቀጥታ መመልከት አይችልም ወይ?

6. የይግባኝ ሥነ ሥርዓት

የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኃላ ሰልጠኞች፡-

- በወንጀል ጉዳይ ላይ ይግባኝ የሚባልበትን ሥርዓት ያብራራሉ፤
- ይግባኝን ለመስማት ስልጣን ስላላቸው ፍ/ቤቶች ይገልጻሉ፡፡

እንደሚታወቀው የይግባኝ መብት የሕገ መንግሥቱም ሆነ አገራችን የተቀበለችው አለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ኮቨናንት መሠረት ያለው የተፈረደበት ተከራካሪ ወገን መብት ነው፡፡ ይሄ መብት ጉዳዩ በታየበት ፍርድ ቤት በተሰጠ ፍርድ ወይም ትዕዛዝ ተበድያለሁ የሚል ወገን የቅሬታ አቤቱታውን ለበላይ ፍ/ቤት በማሰማት ፍርዱ ወይም ትዕዛዙ እንዲሻርለት የሚጠይቅበት እንደመሆኑ መሠረታዊ መብት መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20/6/ ይህንኑ ያመለክታል፡፡

የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 181 የይግባኝ አቤቱታ መርህን ያስቀምጣል የተፈረደበት ተከሳሽ ወይም ተከሳሽ ነፃ በመውጣቱ ወይም በመለቀቁ ምክንያት ይግባኝ ሊባል እንደሚችል ያሣያል፡፡

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መጽሐፍ በ1954 ዓ.ም የወጣ እንደመሆኑ ይግባኝ አቀራረብን በተመለከተ ከቁ 182-183 የተቀመጡት የድሮውን የፍርድ ቤቶች መዋቅርና አደረጃጀት የሚያሣዩ ናቸው በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ያለውን የፌዴራል ሥርዓት ተከትሎ ፍ/ቤቶችም በፌዴራልና በክልሎች ተደራጅተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት በፌዴራል ደረጃ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሲኖሩ በክልሎችም ወረዳ ፍ/ቤት፣ ዞን፣ (ከፍተኛ) ፍ/ቤትና ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች አሉ፡፡

በአዋጅ ቁጥር 25/1988 መሠረት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተሰጠ ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይቀርባል፡፡ ውሣኔው በይግባኝ ከፀና ሁለተኛ ጊዜ ይግባኝ ማለት አይቻልም፡፡ ነገር ግን በውሣኔዎቹ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል አቤቱታ ሲኖር ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ማመልከት እንደሚቻል ተደንግጓል በተመሳሳይ ሁኔታ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ታይቶ በተሰጠ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የሚቀርበው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ነው፡፡ (አንቀጽ 9 እና 13)፡፡

ይግባኝ ማለት መሠረታዊ መብት ቢሆንም ክርክሩ በሂደት ላይ ባለበት ከፍርድ በፊት በሚሠጡ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 184 በተዘረዘሩት ትእዛዞች ላይ ይግባኝ ማለት አይቻልም፡፡ ነገር ግን ጉዳዮ ሲወሰን ትእዛዞቹን ጭምር በመቃወም ይግባኝ ማለት ይቻላል፡፡

የአንድን ተከሳሽ የይግባኝ መብት ያላግባብ ሲያጣብብ የሚታየው በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 185 አተገባበር ላይ አንዳንዴ የሚታዩ ችግሮች ናቸው፡፡ በዚህ ድንጋጌ አንድ ተከሳሽ በእምነት ቃሉ መሠረት የጥፋተኛነት ውሣኔ ከተሰጠበትና ከተቀጣ በቅጣቱ ላይ ካልሆነ በጥፋተኝነት ውሣኔው ላይ ይግባኝ ማለት አይፈቀድም፡፡ ችግሮች የሚታዩት አንድ ተከሳሽ ጥፋቱን አምኗል የሚባለው በምን ሁኔታ ነው ለሚለው ጥያቄ በሚሰጠው ምላሽ ነው፡፡

የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 134(1) ተከሳሹ በክሱ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል ለመሥራቱ በሙሉ ያመነ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ተከሳሹ ጥፋተኛ ነኝ ብሏል በማለት እንደሚመዘግብ ያሣያል፡፡ ከዚህ በግልጽ መረዳት የሚቻለው ለተከሳሽ ክሱን በዝርዝር እንዲያውቀው ማድረግ እንደሚገባ ነው፡፡ ሕገመንግስታችንም በአንቀጽ 20(2) ላይ ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር ለተከሳሽ እንዲነገረውና በጽሑፍም ሊያገኘው መብቱ መሆኑን ያስቀምጣል፡፡ በዚህ መልክ ክሱ ምን እንደሚል በሚገባ ሳይረዳ ተከሳሽ እምነት ክህደት ቢጠየቅና ጥፋተኛ ነኝ ቢል በሕጉ መሠረት ጥፋተኛነቱን አምኗል ለማለት በቂ ነው ማለት አይቻልም፡፡

የችግሩን አሳሳቢነት ያጋጠመ ሁለት ምሣሌዎችን በመጥቀስ ማሣየት ይቻላል፡፡ ዐቃቤ ሕግ የልዩ ወ/መ/ሕ/ቁ. 214/74 አንቀጽ 17 ጠቅሶ (አሁን የተሻረ) ወንጀል በመሥራት ሃሳብ ሰነድ ደልዟል በሚል አንድን አርሶ አደር ይከሳል፡፡ ይህ አርሶ አደር በአካባቢው በመንግሥት ተወርሦ የነበረ የእህል ወፍጮ ገንዘብ ተቀባይ ነበር፡፡ የትምህርት ደረጃው ከመሠረተ ትምህርት ያላለፈ ነው፡፡ ገንዘብ እየተቀበለ ደረሰኝ ሲሰጥ ጽሑፉን ጠበቅ አድርጐ ባለመፃፉ ወይም ካርቦኑ በማርጀቱ ምክንያት ኮፒዎቹ ላይ በጽሑፍ በሚታይ መልኩ ባለመተላለፉ ይህን ለማጉላት ሲል ባደረገው ጥረት ኮፒዎቹ ይደላለዛሉ ይህ ሰው ተከስሶ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ክሱ ተሰጥቶት እና በአስተርጓሚ ተነግሮት እምነት ክህደት ሲጠየቅ ጥፋተኛ ነኝ ይላል፡፡ ፍ/ቤቱ ተከሳሹ ሰነዱን የደለዘው በክሱ ላይ በዝርዝር በተቀመጠው ሁኔታ ወንጀል በመሥራት ሃሳብ ለመሆኑ አልጠየቀውም ተከሳሹ ከክሱ የተረዳው ሰነድ ደልዘሃል መባሉን ብቻ ነበር፡፡ ነገር ግን ጥፋቱን አምኗል ተብሎ 10 ዓመት ጽኑ እሥራት ተፈረደበት፡፡

በ1983 ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ ወቅት በየቦታው የወዳደቁ መሣሪያዎች በአንዱንድ አርሶ አደሮች እጅ ገብተው ነበር፡፡ አንዳንዶቹም ከቀድሞ መንግሥት ወታደሮች በትንሽ ገንዘብ ገዝተው ከሌባና ከአውሬ መከላከያ ይሆነናል በሚል አስቀምጠው ሣለ ለሕግ ወጥ ዓላማ መሣሪያዎቹን ይዘው ተገኝተዋል በሚል ክስ ተመሥርቶባቸው ፍ/ቤት ሲቀርቡ ጥፋተኞች ነን ይላሉ፡፡ ፍ/ቤቶች ተከሳሾቹ ሙሉ በሙሉ በክሱ ዝርዝር የጠቀሱትን ነገሮች ለመፈፀማቸው ጠይቀው ሳያረጋግጡ ጥፋተኛ ነኝ ብሏል በሚል ብቻ ለሕገወጥ ዓላማ መሣሪያ ይዞ መገኘቱ የተረጋገጠበት አጥፊ በሚቀጣበት ቢያንስ የ5 ዓመት ጽኑ እሥራት ቅጣት በሚያስቀጣ አንቀጽ ሥር ጥፋተኛ ተብለው ቅጣት ተወስኖባቸዋል፡፡ እነዚህ ተከሳሾች በአግባቡ ተጠይቀው ቢሆን መሣሪያዎቹን የያዙት ራሳቸውን ከአውሬና ሌባ ለመከላከል እንጂ ለሕገወጥ አላማ አለመሆኑን ባስረዱ ነበር፡፡

አንድ ተከሳሽ ጥፋተኛ ነኝ ሲል ፍ/ቤት ጥፋተኛ ነኝ ያለበትን ምክንያት በዝርዝር ሊጠይቀው እና የክሱን ዝርዝር በሙሉ ማመኑን (ወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.134) ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ከላይ በተጠቀሰው መንገድ ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣ ተከሳሽ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 134 መሠረት ክሱን በሙሉ እንዳመነ ተቆጥሮ

በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 185 እንደተመለከተው በጥፋተኝነት ውሣኔው ላይ ይግባኝ ለማለት ሊከለከል አይገባም፡፡

በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 187 ላይ እንደተመለከተው ይግባኝ የሚጠየቀው ፍርድ በተሠጠ በ15 ቀናት ውስጥ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የሚፈረድባቸው ተከሳሾች ማረሚያ ቤት ስለሚገቡ በሕጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይግባኝ መጠየቅ ያለመጠየቃቸውን ማረጋገጥ የሚያስቸግርበትና ጊዜው አልፏል እየተባለ የይግባኝ ማስፈቀጃ ማመልከቻ ለማቅረብ የሚገደዱበት ሁኔታ አለ፡፡ ችግሩ ሁለት ምክንያቶች ሊከሰት ይቻላል፡፡

1. ተቀጪው እንደተፈረደበት ይግባኝ ማለቱን ለማስታወቅ በ15 ቀን ውስጥ ማመልከቻውን ጽፎ ሊሆን ይችላል፡፡ እስረኛ በመሆኑ ራሱ ፍርድ ቤት ሊወስደው ስለማይችል የሚሰጠው ለማረሚያ ቤቱ ነው፡፡ ማረሚያ ቤቱ በተለያዩ ምክንያቶች በ15 ቀናት ውስጥ ማመልከቻውን ለፍ/ቤት ሣያስተላለፍ የሚቆይበት አጋጣሚዎች አሉ፡፡

2. የይግባኝ መጠየቂያ ማመልከቻው ፍርዱ በተሰጠ 15 ቀን ውስጥም የተፃፈ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፡፡ ነገር ግን ለፍ/ቤት ከረጂም ጊዜ በኋላ ይላክና ማረሚያ ቤቱ ማረጋገጫ እንዲሠጥ ሲጠየቅ ታራሚው መቼ ማመልከቻውን እንደሰጠው ማረጋገጥ የማይቻልበት ሁኔታ ይከሰታል፡፡

የመጀመሪያውን በተመለከተ ጥፋቱ የታራሚው ባለመሆኑ ይግባኙን ለመቀበል ብዙ ላያስቸግር ይችላል፡፡ በሁለተኛው ሁኔታ ግን ታራሚው ይግባኝ መጠየቂያ ማመልከቻውን ፍርድ በተሰጠ በ15 ቀን ውስጥ እንደፃፈ በማድረግ ጊዜው ካለፈ በኋላ ለማረሚያ ቤቱ ሊያቀርብ የሚችልበት ሁኔታ ስለሚኖር ፍ/ቤቱ ተጨማሪ ማጣራቶችን ማድረግ ሊያስፈልገው ይችላል፡፡

ይግባኙ በጊዜው መጠየቁ ከተረጋገጠ ሌላው ሊታይ የሚገባው ፍርዱን የሠጠው ፍርድ ቤት የፍርዱን ግልባጭ ለታራሚው በማረሚያ ቤት በኩል የሚያደርስበት ጊዜ ነው፡፡

ታራሚው (ይግባኝ ባይ) የፍርድ ግልባጭ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማመልከቻውን ፍርድ ለሠጠው ፍ/ቤት ማቅረብ ይኖርበታል (ቁ. 189)።

በዚህ ረገድም ችግሮች ይታያሉ ታራሚው የፍርድ ግልባጭ የሚደርሰው በማረሚያ ቤት በኩል እንደመሆኑ መጠን ፍርድ ግልባጩ ደረሰው የሚባለው የመዝገብ ሹመ (ሬጅስትራሩ) ግልባጩን ለማረሚያ ቤቱ የላከበት ቀን ነው ወይንስ ማረሚያ ቤቱ ለአመልካቹ አስፈርሞ የሚሠጥበት ቀን ነው የሚለው በተግባር ቀላል ሆኖ አይታይም። ሕጉ የፍርድ ግልባጭ ለማረሚያ ቤቱ የደረሰበትን ቀን እንደ መነሻ የወሰደ ይመስላል፡ (ቁ 187(1))ይህም ያለ ምክንያት አይደለም። ታራሚው የሚገኝበት ማረማያ ቤት ፍርድ ግልባጩ እንደደረሰው በእለቱ ለአመልካች ይሠጣል በሚል እሳቤ ነው። አንዳንዴ ግን እውነታው ከዚህ የተለየ ነው። በተለያዩ ምክንያቶች የፍርድ ግልባጭ ለማረሚያ ቤቱ ጽ/ቤት ደርሦም በእለቱ ለታራሚው ሳይሰጥ ሊቆይ ይችላል በዚህ የተነሳም ታራሚው የይግባኝ ማመልከቻውን ፍርድ በደረሰው 30 ቀናት ውስጥ (ለማረሚያ ቤት ከደረሰበት ቀን ጀምሮ እየተቆጠረ ማለት ነው) አላቀረበም የሚባልበት ሁኔታ ካለ ለመዘግየቱ ተጠያቂው ማን መሆኑ ሊጣራ የሚገባው ከመሆኑም በላይ የፍርድ ግልባጭ ለታራሚው ደረሰ ሊባል የሚገባው ለራሱ የደረሰበት እንጂ ለማረሚያ ቤቱ የተላከበት ቀን ሊሆን አይገባውም።

ከዚህም በተጨማሪ የፍርድ ግልባጭ ለማረሚያ ቤት በደረሰበት ቀን ለታራሚውም ደርሦ ታራሚው የይግባኝ ማመልከቻውን ሠላሣ ቀን ከመሙላቱ በፊት ጽፎ ለማረሚያ ቤቱ ቢያስረክብም ለፍ/ቤት ዘግይቶ የሚደርስበት አጋጣሚም አለ። በታራሚው በኩል ለመዘግየቱ አስተዋጽኦ እስከሌለ ድረስ ይግባኙ ሊታይ የሚገባው ነው፡ የፈረደው ፍ/ቤት ወይም ማረሚያ ቤቱ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈው በእነሱ ምክንያት መሆኑን ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ካረጋገጡ የይግባኝ ማስፈቀጃ እንዲቀርብ ማድረግ ብዙም ትርጉም ያለው አይደለም።

የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 192 የይግባኝ ክርክር ስለሚሠማበት ሁኔታ የሚደነግግ ነው የይግባኝ ክርክር በችሎት የሚሠማ እንደመሆኑ በቃል የሚደረግ ነው፡ የግራ ቀኙም ክርክር በአንድ ቀጠሮ የሚጠናቀቅ ነው ይህን ሕግ ተግባራዊ በማድረግ ረገድ በሕግ ባለሙያ

በማይታገዙ ግለሰቦች በኩል ችግር አለ፡፡ በቃል ክርክራችንን ማሰማት አንችልም እያሉ በጽሑፍ መልሳቸውን ያቀርባሉ በግድ በቃል ክርክራችሁን አሰሙ ማለት መብታቸውን ማጣበብ ይሆናል በሚል መልሳቸውን በጽሑፍ መቀበል የማይታለፍ ይሆናል የሌላውን ወገን የመ/መልስ መስማት አስፈላጊ በሚሆን ጊዜ ቀጠሮ ለመለወጥ ምክንያት ይሆናል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው በሕግ ተለይተው ከተገለፁ ወንጀሎች ውጭ አንድ ተከሳሽ ጉዳዩ በሌለበት አይታይም በይግባኝ ደረጃ ግን ወንጀሉ ምንም ቢሆን መ/ሰጭ ካልቀረበ ይግባኙ በሌለበት መስማቱ ይቀጥላል (ቁ.193) የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በዋናነት የሚመረምረው በሥር ፍ/ቤት የቀረቡትን ማስረጃዎች ነው ነገር ግን ተጨማሪ ማስረጃ መስማት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ምክንያቱን ጽፎ ማስረጃውን መቀበል እንደሚችል የፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 194 ያሣያል፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ይህንን ለፍ/ቤቱ የተሠጠን ሥልጣን ለመጠቀም በመፈለግ በሥር ፍ/ቤት ሊያቀርቡ ሲችሉ ያለፉት ማስረጃ እንዲቀርብላቸው የሚጠይቁበት ጊዜ ስላለ ፍ/ቤቱ ማስረጃውን ከመቀበሉ በፊት የማስረጃውን ወሳኝ መሆን በጥንቃቄ ማገናዘብ ይገባዋል የይግባኝ ክርክር ከተጠናቀቀ በኋላ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሠረዝ የጥፋተኝነት ውሣኔ በማጽናት ቅጣት መቀነስ ወይም በሥር ፍ/ቤት በነፃ የተለቀቀን ተከሳሽ ጥፋተኛ በማድረግ መቅጣት ይቻላል፡፡ ወይንም ደግሞ ጉዳዩ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ እንደገና እንዲታይ ማዘዝ ይችላል (ቁ. 195) ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅጣት መቀነስ ወይም መጨመር የሚችል ቢሆንም ቅጣት በዛብኝ ብሎ ይግባኝ በጠየቀ ይግባኝ ባይ ላይ ቅጣት መጨመር ባልተጠየቀ ዳኝነት መፍረድ ስለሚሆን ተገቢ አይደለም፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ጥፋቱን አምኗል ተብሎ የተቀጣ ይግባኝ ባይ በጥፋተኝነት ውሣኔ ላይም ይግባኝ ቢጠይቅ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መውሰድ ያለበት እርምጃ ምንድነው?

2. በቅጣት ውሳኔ ላይ ቅጣቱ በዝቷል ተብሎ በቀረበ ይግባኝ ዐ/ሕጉ መልስ ሲሰጥ ፍርድ የሰጠው ፍ/ቤት በሕጉ ከተደነገገው ቅጣት አሳንሶ የቀጣው ስለሆነ ቅጣት

ሊጨመርበት ይገባል ቢልና ሕጉም ሲታይ እውነትም በሕጉ ከተደነገገው በታች ሆኖ ቢገኝ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ምን ማድረግ አለበት? ለምን?

3. በወንጀል ይግባኝ ጊዜ አያስቀርብም የሚል አሰራር ይቻላል ወይ?

7. ቅጣት፣ ገደብ እና አመክሮ

የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ስልጠና በኃላ ሰልጣኞች፡-

- ወጥነት ያለው የቅጣት አወሳሰንን ጠቀሜታ እና በምን መልኩ ሊረጋገጥ እንደሚችል ያብራራሉ፤
- ከህዝበዊ መብት መሻር ምን እንደሆነ እና የሚያስከትለውን ህጋዊ ውጤት አውቀው ተግባራዊ ያደርጋሉ፤
- ውሳኔ እና ቅጣት ሊገደቡ የሚችሉባቸውን ህጋዊ ምክንየቶች ለይተው በስራ ላይ ያውላሉ፤
- አመክሮ ሊፈቀድ የሚችልባቸውን መንገዶች አውቀው በተግባር ይተረጉማሉ፡፡

1. <u>የቅጣት አፈጻጸም</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 1 ሥር እንደተገለፀው የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግሥት የሕዝቦቿንና የነዋሪዎቿን ወይም ደህንነት፣ ሥርዓት፣ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው ግቡ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህም ስለወንጀሎቹና ቅጣታቸው በማሳወቅና በማስጠንቀቅ ከዚህም ካለፈ በመቅጣት ነው፡፡

ቅጣት በመሠረቱ ተቀጭው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲታቀብ ተቀጪውን ለሚያዩ ደግሞ ራሳቸውን ከወንጀል ተግባር እንዲያርቁ ማስተማሪያ ነው በዚህ ሁኔታ ቅጣት

ከሚወሰንባቸው አጥፋዎች ጋር ሲነፃፀር ቁጥራቸው በጣም ጥቂት የሚሆኑ አጥፊዎች ላይ የፈፀሙት ወንጀል እጅግ ከባድ ከሆነና ቅጣትን ለመቀነስ የሚያስችል ምክንያት ሳይገኝ ሲቀር የሞት ቅጣት የሚወሰንባቸው አሉ፡፡ በእነዚህ ወገኖች ላይ የመጨረሻው ቅጣት መወሰኑ ግን በሕጋችን የቅጣትን አጥፊዎችን የማረሚያና ሌሎችንም የማስተማር ዋነኛ ግቡን የሚያስቀር አይሆንም፡፡

በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ ወጥነት ከሌላቸውና የፍ/ቤቶችን ተገማችነት ጥያቄ ውስጥ እያስገቡ ካሉ ጉዳዮች አንዱ ቅጣት በመወሰን ረገድ ያለውን የተዘበራረቀ አሠራር ነው፡፡ በወንጀል ሕጋችን መግቢያ እና አንቀጽ 88 ላይ የቅጣት አወሳሰንን ትክክለኛነትና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥም ሆነ ለመቆጣጠር የሚያስችል የቅጣት አወሣሰን መመሪያ እንደሚወጣ የተጠቀሰ ስለሆነ መመሪያው ሲወጣ ችግሩን ሊቀርፈው ይቻላል ተብሎ ይገመታል፡፡

በወንጀል ሕጋችን ሁለተኛ መጽሐፍ የወንጀል ቅጣትና አፈፃፀሙ በሚል ርእስ በአንቀጽ 87 ሥር በሕጉ የተመለከቱት ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ሕጉ ሊደርስበት ያሰበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በሕጉ መንፈስ መሠረት መፈፀም እንዳለባቸው መርህ አስቀምጧል፡፡ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎቹም ሰብአዊ ክብር በሚጠብቅ መንገድ መፈፀም ይኖርባቸዋል ይላል፡፡

ፍ/ቤቶች በቅጣት አወሣሠን ወጥነት ረገድ የሚከተሉት መመሪያ ያለመኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ በሌላ በኩል ግን ቅጣትን ለመወሰን በአንቀጽ 87 ከተቀመጠው በተጨማሪ በአንቀጽ 88 ላይ ፍ/ቤቶች ሊከተሉት የሚገባቸውን ነገሮችን ይዘረዝራል፡፡ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኝነት መጠን ያለፈ የሕይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሳሱትን ምክንያቶችና የሃሳቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ የትምህርቱን ደረጃ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነት የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን ነው፡፡

ፍ/ቤቶች ቅጣት ሲወስኑ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ፍሬ ሃሳቦች ማገናዘባቸውን ከአንቀጽ 82 ጀምሮ እስከ አንቀጽ 86 ሥር ያሉትን የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ

ምክንያቶችን መመርመራቸውን በቅጣት ውሣኔዎቻቸው ላይ ይጽፋሉ፡፡ ነገር ግን በየዳኛው የህሊና ግምት ከላይ ለተዘረዘሩት ነገሮች የሚሠጠው ክብደት የተለያየ ከመሆኑ አንፃር በአንድ ዓይነት ወንጀል ተከሰው አፈፃፀማቸውና ማስረጃዎቹ በእጅጉ ተመሳሳይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚሠጠው የእሥራት ቅጣት መጠን አንድ ዓይነት እንዲሆን ባይጠበቅም የልዮነቱ ስፋት ግን አሣሣቢ በመሆኑ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡

የወንጀል ቅጣቶች በዋነኛነት ሦስት ዓይነት ናቸው እነዚህም የገንዘብ መቀጮ/ቅጣት የግዴታ ሥራና ነፃነትን የሚያሣጡ ቅጣቶችና የሞት ቅጣት ናቸው፡፡

በሕጉ ልዩ ክፍል የወንጀል ድርጊቱ በገንዘብ መቀጫ እንደሚያስቀጣ በተደነገገ ጊዜ ወይም ደግሞ ቅጣቱ በእሥራት ወይም የገንዘብ ቅጣት በአማራጭ ሲሆን የገንዘብ መቀጮ መወሰን ይቻላል፡፡

የገንዘብ መቀጮ እንዲከፍል የተወሰነበት አጥፊ መቀጮውን ወዲያው መክፈል ይኖርበታል (አንቀጽ 93) መክፈል ካልቻለ ግን እስከ ሦስት ዓመት ሊደርስ የሚችል ጊዜ ፍርድ ቤቱ ሊሠጠው እንደሚችልና ገንዘቡን ጥቂት በጥቂት እንዲከፍል እንደሚያደርግም ተመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ መቀጮውን እንዲከፍል ለማድረግ ተቀጪውን ዋስ እንደሚያስጠራው ወይም መያዣ እንዲሠጥ በማድረግ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ካልከፈለ ግን የዋስትናውን ገንዘብ ገቢ እንዲሆን እንደሚያዝ አንቀጽ 94 ይደነግጋል፡፡ ከዚህም አልፎ ተቀጪው መቀጮውን መክፈል የማይችል ከሆነ መቀጮውን በሥራ በመለወጥ ለሕዝብ አገልግሎት ድርጅት ወይም ለመንግሥት በሥራ በማገልገል እንዲከፍል ወይም ደግሞ የግዴታ ሥራ እንዲሠራ ፍ/ቤት ሊወስን ይችላል፡፡

ሕጉ የገንዘብ መቀጮ ለተወሰነበት አጥፊ ከላይ የተመለከተውን ሠፊ ዕድል ሰጥቶት እያለ መቀጮውን እስኪከፍል ማረፊያ ቤት ይቆይ እየተባለ አልፍ አልፎ የሚሠጠው ትእዛዝ በፍፁም የሕግ መሠረት የሌለው አሠራር ነው፡፡

ከስድስት ወር በማይበልጥ እሥራት በሚያስቀጡ ቀላል ወንጀሎች ጥፋተኛ የተባለ ሰው ለህብረተሰቡ አደገኛ ካልሆነ በእሥራት ቅጣት ምትክ የግዴታ ሥራ እንዲሰጡ ሊወሰንበት ይቻላል (አንቀጽ 103) በዚህ ሁኔታ ተቀጭው ሠርቶ ከሚያገኘው ገንዘብ ሲሶው ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል፡፡ ከዚህም ሌላ የግዴታ ሥራው የተቀጪውን ነፃነት በአንድ የተወሰነ ቦታ ከመገደብ ጭምር ሊወሰንበት ይቻላል፡፡ ይህ አሠራር ግን በፍ/ቤቶቻችን የተለመደ አይደለም፡፡

ሌላው የቅጣት ዓይነት የእሥራት ወይም የግል ነፃነትን የሚያሣጣ ቅጣት ነው፡፡ ይህ ቅጣት ቀላል እሥራት ወይም ጽኑ እሥራት ሊሆን ይችላል፡፡ ቀላል እሥራት ከ10 ቀን እስከ 3 ዓመት ሊደርስ የሚችል ሲሆን እንደነገሩ ሁኔታ እስከ 5 ዓመትም ሊዘልቅ ይችላል፡፡ ይህ የሚሆነው በቀላል እሥራት የሚያስቀጡ የተደራረቡ ወንጀሎች ሲኖሩ ወይም አጥፊው በተደጋጋሚ ሲቀጣ ነው፡፡ (አንቀጽ 106)
የጽኑ እሥራት ቅጣት የሚወሰነው ከባድ ወንጀል በፈፀሙና ለህብረተሰቡ አደገኛ በሆኑ ወንጀለኞች ላይ ነው(አንቀጽ 108)፡፡ የጽኑ እሥራት ቅጣት ከ1 ዓመት እስከ 25 ዓመት የሚደርስ ሲሆን በህጉ ተደንግጎ ሲገኝ እስከ እድሜ ልክ እሥራት ይሆናል፡፡ ለምሳሌ ያህል በወ/ሕ/ቁ 539 ሥር በከባድ የሰው ግድያ ወንጀል ጥፋተኛ የተባለ ሰው የሚቀጣው በጽኑ እሥራት ነው፡፡ በዚህ ሕግ ሥር ቅጣቱ እድሜ ልክ ወይም ሞት ስለሆነ የጽኑ እሥራቱ ቅጣት እድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ይሆናል ማለት ነው፡፡

የጽኑ እሥራት ቅጣት የተፈረደበት አጥፊ በሕዝባዊ መብቶቹ ከመሥራት ይሻራል (አንቀጽ 124) ይህ ከመብት የመሻር ቅጣት ለዘወትር ሊሆን እንደሚችል ለጊዜው ከሆነ ደግሞ ከስድስት ወር እንደማያንስና ከአምስት ዓመት እንደማይበልጥ በአንቀጽ 124 ላይ ተደንግጓል፡፡

የጽኑ እሥራት ቅጣት ከሕዝባዊ መብት የመሻርን ጉዳይ ማስከተሉ ግዴታ ሆኖ ሣለ ፍርድ ቤቶች አብዛኛውን ጊዜ ይህንን በፍርድ ውስጥ ሲያካትቱ አይታይም፡፡

ሦስተኛው የቅጣት ዓይነት የሞት ቅጣት ነው፡፡ ይህን ቅጣት ለመወሰን የተወሰኑ ቅድመ ሁኔታዎች ሊሟሉ ይገባል ወንጀሉ ፍፃሜ ያገኘና እጅግ ከባድ መሆን አለበት፡፡

ወንጀለኛውም አደገኛ መሆኑና ቅጣትን የሚያቀል ምክንያት የሌለ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል ከዚህ በተጨማሪም ወንጀለኛው ወንጀሉን በፈፀመበት ጊዜ እድሜው 18 ዓመት የሞላው መሆን አለበት (አንቀጽ 117) የሞት ቅጣት በምህረት ወይም በይቅርታ መለወጡ ሳይረጋገጥ እንዲሁም በሀገሪቱ ርዕሰብሔር ሳይፀድቅ ተፈፃሚ አይሆንም።

የወ/ሕ/ቁ 119 በፍፁም ኢ-ኃላፊነት ወይም በከፊል ኃላፊነት ላይ የሚገኝ ወይም በጽኑ የታመመ ሰው ወይም ያረገዘች ሴት በዚህ ሁኔታ ላይ እስከሚገኙበት ጊዜ ድረስ የሞት ቅጣት ታግዶ እንደሚቆይ ይደነግጋል።

ከድንጋጌው መገንዘብ የሚቻለው ወንጀለኞቹ የሞት ቅጣት ያስከተለባቸው ድርጊት ከፈፀሙና ከቅጣት በኋላ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ውስጥ የወደቁ መሆናቸውን ነው።
ሌላው የሞት ቅጣት የሚለወጥበት ሁኔታ ነፍሰጡር የሆነች አጥፊ ሕይወት ያለው ልጅ ወልዳ ልጁን ማሳደግና መመገብ ሲኖርባት ነው። ይህ ሁኔታ ሲከሰት የሞት ቅጣቱ በእድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ይለወጥላታል(አንቀጽ 120)።

2. <u>ገደብ</u>

ከላይ እንደተመለከተው ቅጣት የሚወሰነው በዋነኛነት አጥፊውን ለማረምና ለሌላውም ትምህርት እንዲሆን ነው።

የቅጣት ውሣኔን በገደብ ማቆም እና አጥፊው ወደ ማህበራዊ ኑሮ እንዲመለስ ማድረግ አጥፊው ከእስር ውጭ ሆኖ ፀባዩ ሊታረምና ሊሻሻል ይችላል ተብሎ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ የሚፈፀም ነው። ወንጀለኛው ቅጣቱ ተገድቦለት እያለ ፀባዩ ያልታረመና ያልተሻሻለ መሆኑ ሲታወቅ ቅጣትን በመገደብ የተሰጠው ውሣኔ ይሻራል። (አንቀጽ 190) (194 (2)(ሐ))።

አንድ አጥፊ ጥፋተኛ የተባለበት ወንጀል መቀጮ ግዴታ ሥራ ወይም ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት የሚያስቀጣ ሲሆን ወንጀለኛው ለወደፊቱ ፀባዩን ለማረም የሚችል መሆኑ ሲታመንበት የጥፋተኝነት ውሣኔ ከተሠጠ በኋላ የፈተና ጊዜ በመስጠት ቅጣት

ሣይወሰን ማቆየት ይቻላል (191) ወንጀለኛው በተሠጠው ጊዜ ውስጥ ፀባዩ መልካም ሆኖ ከተገኘ ፍርዱ እንዳልተሠጠ ይቆጠራል፡፡

የቅጣት ውሳኔ ተሠጥቶ የተገደበለት ወንጀለኛ ግን ፍርዱ በወንጀለኞች መዝገብ ተመዝግቦ እንደሚቀመጥ ተመልክቷል፡፡

ቅጣትን ወይም የጥፋተኝነትን ፍርድ ማገድ እንደሚቻል ከላይ በተጠቀሱት የሕግ ድንጋጌዎች ላይ የተጠቀሰ ቢሆንም ቅጣትን መገደብ የማይቻልባቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡ አንድ ወንጀለኛ ከአምስት ዓመት በላይ ጽኑ እሥራት የሚፈረድበት ከሆነ ቅጣትን መገደብ እንደማይቻል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ላይ ተደንግጓል፡፡ ፍርድ ቤቶች ግን አልፎ አልፎ ይህንን በመጣስ ከአምስት ዓመት በለይ ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ የፈረዱበትን ወንጀለኛ ቅጣት ሲገድቡ ይታያል፡፡

በአንድ ወቅት በቀይሽብር ለተፈፀሙ ወንጀል በግብረአበርነት የተከሰሱ ሰዎች ላይ የአንድ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በቀድሞው የወ/መ/ሕ/ቁ 522 ሥር የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቶ በእያንዳንዳቸው ላይ ከ10 ዓመት በላይ ቅጣት ከወሰነ በኋላ ቅጣቱን አግዶታል፡፡ ይህ በፍፁም ሕግን ያልተከተለ በመሆኑ በይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ቀርቦ ፍርዱ ተሽሮ ወንጀለኖቹ ቅጣቱን እንዲፈጽሙ ተደርጓል፡፡ በመርህ ደረጃ ቅጣት መገደብ የሚቻል ቢሆንም በወ/ሕ/ አንቀጽ 194 ላይ ከተደነገገው በተጨማሪ አንዳንድ ሁኔታዎች በቅድሚያ ሊሟሉ ይገባል፡፡ የወንጀለኛው ቀድሞ ታሪኩና ፀባዩ (አንቀጽ 196) ሲታይ ገደቡ ጥሩ ውጤት የሚያስገኝ መሆኑ ሲገመት በጥፋቱ ያደረሰውን ጉዳት እንደሚክስ ዋስትና (ማረጋገጫ) ሲሰጥ (197) ከዚህም ሌላ በገደብ እንዲቆይ ሲወሰን ስለተከሳሹ የፀባይ አመራር ደንብ በዝርዝር ፍ/ቤቱ እንደሚያስቀምጥና ጥፋተኛው ላይም ጠባቂነት ሥልጣን በተሠጠው አካል ቁጥጥር እንዲደረግበት እንደሚያዝ ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም የጥፋተኝነት ወይም የቅጣት ውሣኔን ለማገድ በርካታ ነገሮች ሊሟሉ የሚገባቸው በመሆኑና በሕግ የተጠቀሱት በገደብ የተለቀቁን ተከሳሽ የሚቆጣጠሩ አካላት ባለመኖራቸውም ጭምር ይመስላል በገደብ የመልቀቅ ውሣኔዎች ብዙ አይደሉም፡፡

ቢኖሩም ደግሞ ለተወሰነ ጊዜ በገደብ መለቀቁን በፍርድ ላይ ከማስፈር ውጭ በሕጉ በዝርዝር በተመለከተው አኳኋን ሲሰራ አይታይም፡፡

3. <u>አመክሮ</u>

አመክሮ የቅጣት ማስተማሪያነት ከሚገልጽባቸው ሁኔታዎች አንዱ ነው ማለት ይቻላል፡፡ አንድ ተቀጪ ለፈፀመው ወንጀል የተፈረደበትን የእሥራት ጊዜ ሙሉ በሙሉ ከመፈፀሙ በፊት የተወሰነ ጊዜ በመስጠት ቀሪውን የእስር ጊዜ ከእስር ውጪ ሆኖ እንዲያጠናቅቅ የማድረግ ሥርዓት ነው አንድ ተቀጪ በአመክሮ ሊፈታ ይችል ዘንድ በወንጀል ሕጉ የተደነገጉት ቅድመ ሁኔታዎች ሊሟሉ ይገባል፡፡
የወ/ሕ/ቁ 201 በተወሰነ ገደብ በአመክሮ መፈታትን አስመልክቶ መርህ አስቀምጧል፡፡ በአመክሮ መፈታት የተቀጪውን ፀባይ ማሻሻያ እና ወደደንበኛው ማህበራዊ ኑሮ መመለሻ ሆኖ መቆጠር እንደሚገባው ይገልፃል፡፡

በአመክሮ ለመፈታት ይቻለው ዘንድ አንድ ተቀጪ ከተፈረደበት ቅጣት 2/3ኛውን መፈፀም ይኖርበታል፡፡ የዕድሜ ልክ ጸኑ እሥራት ፍርደኛ ከሆነም ሃያ አመት ታስሮ ነው ጥያቄውን ማቅረብ የሚችለው፡፡ በአመክሮ የመፈታት ጥያቄ በተቀጪው ወይም “አግባብ ባለው አካል ለፍርድ ቤቱ ይቀርባል” (አንቀጽ202(1) “አግባብ ያለው አካል” ማነው የሚለውን ሕጉ አይመልስም እንደሚታወቀው በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኛ ተብሎ እሥራት የተወሰነበት ሰው የሚቆየው ማረሚያ ቤት በመሆኑና የአመክሮ ጥያቄንም ለፍ/ቤት የሚያቀርበው ይኸው ተቋም በመሆኑ አግባብ ያለው አካል ማረሚያ ቤት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሕጉ ግን ምናልባትም ወጣት ጥፋተኞች የሚቆዩበትንም ተቋማትና ሌሎችንም ታሳቢ ያደረገ ይመስላል፡፡

አመክሮን በሚመለከትም ማረሚያ ቤት ስለተቀጪው ፀባይ (አንቀጽ 202 (1) (ሀ)(ለ)) አጣርቶ ለፍ/ቤት ከሚልከው በተጨማሪ ተቀጪው ለደረሰው ጉዳት በተቻለ መጠን ሊከፍል የሚጠበቅበትን በፍርድ ቤት በተወሰነው መሠረት ወይም ከተበዳዩ ጋር በተደረገ ስምምነት መሠረት ካሣ ለመክፈሉ ማረጋገጫ ማቅረብ እንደሚገባ በአንቀጽ 202(1)(ለ) ላይ ተመልክቷል፡፡ ነገር ግን በተግባር ይህ አይደረግም፡፡ ማረሚያ ቤቱ

የተቀጪውን ፀባይ መሻሻል ፍርም ሞልቶ ከላከ ያለተጨማሪ ጥያቄ እስረኛው እንዲለቀቅ ይደረጋል።

ሌላው በሕጉ ላይ የተመለከተውና በፍርድ ቤቶች ግን ሲተገበር የማይስተዋለው ጥፋተኛው ሲፈርድበት ቅጣቱን ከመፈፀሙ በፊት ቀደም ብሎ ሊለቀቅ እንደሚችልና ይህን እድል ለማግኘት ሊፈጽማቸው የሚገቡ ነገሮች እንደሚገለፁለት የተመለከተው ነው።

እንደ ገደብ ውሣኔ ሁሉ በአመክሮ የሚለቀቅ ተቀጪም የፈተና ጊዜ ይሠጠዋል ይህም ማለት በተሠጠው የፈተና ጊዜ ውስጥ ፀባዩ ባይሻሻል ወይም ሌላ ወንጀል ሲፈጽም ቢገኝ (አንቀጽ 200 እና 206) በአመክሮ እንዲፈታ የተሰጠው ትእዛዝ ተነስቶ ተመልሦ እንዲታሠር ይደረጋል። በአመክሮ ቀርቶለት የነበረውን ቀሪ ቅጣትና ለአዲሱ ጥፋት የተወሰነበትን ጊዜ ይታሠራል።

የፈተናው ጊዜ እንደወንጀሉ ክብደት እየታየ የሚሠጥ ነው። በመርህ ደረጃ የፈተና ጊዜ የሚለው ሳይፈፀም የቀረው የእሥራት ጊዜ ማለትም 1/3ኛው የቅጣት ዘመን ነው። በአመክሮ ተቀጪው እንዲለቀቅ ፍ/ቤት ሲያዝ የፈተናው ጊዜ ቢያንስ ሁለት ዓመት ሲሆን ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ነው። በአመክሮ የመፈታት ዕድል ያገኘው ተቀጪ የዕድሜ ልክ እስረኛ ከሆነ ግን የፈተና ጊዜው ከ5 ዓመት ማነስ ና ከ7 ዓመት መብለጥ የለበትም (አንቀጽ 204)።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. የጽኑ እስራት ፍርደኛ በተለይ በእስር ላይ እያለ በፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ስለ መብት መሻሩ ሳይጠቀስ ቢዘለል ለምስክርነት መቆጠር ይችላል ወይ?

2. በገደብ ለመለቀቅ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች ምንድናቸው?

3. ለተበደለ ወገን ካሳ ያልከፈለ ተከሳሽ በወ/ህ/አ 197/2 መሰረት በገደብ ሊለቀቅ ይችላል ወይ?

4. በገደብ ለመለቀቅ በራስ ዋስትና መፈረም በወ/ህ/አ 197/2 መሰረት በቂ ሊሆን ይ ችላል ወይ?

5. በአመክሮ ለመለቀቅ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች ምንድናቸው?

ዋቢ ጽሁፎች

1. Andrew West, Yvon Desdevises et al, *The French Legal System, an Introduction*, (London: Fourmat Publishing, 1993).

2. **ብ/ጄኔራል ታጠቅ ታደሰ፣ *የማስረጃ ሕግ መሠረተ ሃሳቦች*፤ (አዲስ አበባ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መጻህፍት ማዕከል፣ 1ኛ ዕትም፣** 1996).

3. Bryan A. Garner(ed.), *Black's Law Dictionary*, (Washington: West Publishing Co., 8th ed ., 2004).

4. Jerold H. Israel, and Wayne R La Fave, *Criminal Procedure, Constitutional Limitations in anut shell*, (St. Paul: West Publishing Co., 8th ed., 2001).

5. John N. Ferdico, *Criminal Procedure*, (Stamford: Wadsworth Group, 8th ed., 2002).

6. J.W.Ceil Turner, *Kenny's Outlines of Criminal Law*, (New Delhi: Universal Law Publishing Co. Pvt. Ltd., 19thed., Second Indian Reprint, 2004).

7. Marvin Zalman and Larry Siegel, *Key Cases and Comments on Criminal Procedure*, (St. Paul: West Publishing Co., 1994 ed., 1995).

8. Stanley Z Fisher, *Ethiopian Criminal Procedure, a Sourcebook,* (Addis Ababa: the Faculty of Law Haileselassie I University and Oxford University Press, 1969).

9. **ፀሐይ ወዳ፣ *የወንጀል ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች*፣(አዲስ አበባ፣ *1994 ዓ.ም*).**

10. Wayne R. LaFave and Jerold H. Israel, *Criminal Procedure*, (St. Paul: West Publishing Co., 4th ed., 2004).